# ወንጌላት

ትምህርት
አንድ

## የወንጌላት መግቢያ

ተርጓሚ፣ እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM
MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

© 2012 by Third Millennium Ministries

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced in any form or by any means for profit, except in brief quotations for the purposes of review, comment, or scholarship, without written permission from the publisher, Third Millennium Ministries, Inc., P.O. Box 300769, Fern Park, Florida 32730-0769.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ጎብኙ፡፡

ማውጫ

1. መግቢያ
2. ስነ-ጽሁፋዊ ዳራ (ባህርይ)
   ሀ. ዓይነት
      1. ታሪካዊ ትረካ
      2. ግሪኮ-ሮማዊ ታሪክ
      3. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪካዊ ትረካ
   ለ. አስተማማኝነት/ተዓማኒነት
      1. መረጃን የማግኘት ዕድል
      2. ግልጽነት
      3. ማረጋገጫ
      4. ስልጠና
      5. ነገረ-መለኮታዊ ቁርጠኝነት
      6. መንፈስ ቅዱስ
3. በቤተክርስቲያን ያለቸው ስፍራ
   ሀ. አፃፃፍ
      1. ተመሳሳይነት
      2. የአፃፃፍ ፅንሰ-ሃሳብ
      3. እርግጠኝነት
   ለ. እውነተኝነት
      1. ተአማኒ-ፀሐፍት
      2. ሐዋርያዊ ይሁንታ
      3. የቤተክርስቲያን ምስክርነት
4. አንድነት
   ሀ. ተመሳሳይ ታሪክ
   ለ. ኢየሱስ
      1. ማስረጃዎች
      2. መዝገበ ቃላት
      3. ደረጃዎች
5. ልዩ ልዩ ዓይነት
   ሀ. የማንሸሻቸው (ግልፅ) ችግሮች
      1. ቅደም ተከተል
      2. አለማካተት
      3. ልዩ ልዩ ሁነቶች
      4. ልዩ ልዩ ዜቤዎች (ንግግሮች/ቋንቋዎች)
   ለ. ልዩ ትኩረት
      1. በማቴዎስ ኢየሱስ ማን ነው?
      2. በማርቆስ ኢየሱስ ማን ነው?
      3. በሉቃስ ኢየሱስ ማን ነው?

4. በዮሐንስ ኢየሱስ ማን ነው?

6. ማጠቃለያ

# መግቢያ

የምንሰማቸው ዜናዎች ለሕይወታችን ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ አስተውላችኋል? ስለምንኖርበት ዓለም የምናገኛቸው ጠቃሚ መረጃዎች አስተሳሰቦቻችንን፣ እሴቶቻችንን፣ ዕቅዶቻችንን እና የሕይወታችንን በርካታ ገፅታዎች ተፅዕኖ ያሳድሩበታል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የምንሰማቸው ዜናዎች ንፅረተ-ዓለማችንን ከመለወጥ አንፃር እጅግ ወሳኝነት አላቸው፡፡

እንግዲህ፣ ስለዚህ ነገር ማሰብ ካቆምን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ የዜናዎች ወይም የታሪኮች መድብል ብቻ ሆኖ ይቀራል፡፡ በታሪክ ዘመን መካከል ከእግዚአብሔር ህዝብ ጋር የተያያዙ ክፉና በጎ ዜናዎችን መዝግቦልናል፡፡ እነዚህን ታሪኮች በምናነብበት ወቅት፣ በበርካታ መንገዶች ይለውጡናል፡፡

ያለጥርጥር፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ለእኛ የሚያስተላልፉልን ምርጥ ዜና "የምሥራች" ወይንም "ወንጌል" ብለን የምንጠራውን ዝርዝር ዘገባ ነው፡፡ ዘገባውም ሕይወት ለዋጭ የሆነውን የጌታችንንና መድሃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወት ታሪክ ያዘለ ነው፡፡

ወንጌላት በሚል ርዕስ ከምንመለከተው ትምህርታችን ይህ የመጀመሪያው ነው፡፡ በዚህ ተከታታይ ትምህርት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት የሚተርኩትን የማቴዎስን፣ የማርቆስን፣ የሉቃስንና የዮሐንስን መጻሕፍት እንዳስሳለን፡፡ በዚህ "የወንጌላት መግቢያ" በተሰኘው ትምህርት፣ የእነዚህን መጻሕፍት መግቢያዎች የምንመለከት ሲሆን ይህም የበለጠ እንድንረዳቸውና በዚህ ዘመን ሕይወታችንም ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንድናደርጋቸው ያስችለናል፡፡

በወንጌላት ላይ በምናቀርበው የመግቢያ ሃሳብ፣ አራት ወሳኝ ጉዳዮችን እንዳስሳለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ወንጌላትን ከስነ-ጽሁፋዊ ባህርያቸው አንጻር እንመለከታቸዋለን፡፡ ሁለተኛ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያላቸውን ስፍራ እናያለን፡፡ ሦስተኛ፣ በወንጌላት መካከል ያለውን አንድነት እንቃኛለን፡፡ አራተኛ ደግሞ፣ አንዳቸውን ከሌላቸው የሚለያቸውን እንቃኛለን፡፡ በስነ-ጽሁፋዊ ባህርያቸው እንጀምር፡፡

## ስነ-ጽሁፋዊ ባህርይ

***አብዛኛውን ጊዜ፣ አንድን ጽሁፍ በምናነብበት ወቅት፣ የምናነበው ጽሁፍ ምን ዓይነት ስነጽሁፋዊ ባህርይ እንዳለው የተወሰነ ሃሳብ ይኖረናል፣ ያም እንዴት እንደምናነበውና ከምንባባችን ምን እንደምንጠብቅም ይመራናል፡፡ እንግዲያው፣ ለምሳሌ፣ ታሪካዊ ልብ ወለድ የምታነብብ ከሆነ፣ እውነተኛ ታሪክ እንደሆነ በማሰብ ልትሳሳት አይገባም፡፡ ወይም የአጫጭር ታሪኮችን መድብል የምታንብብ ከሆነ፣ ተከታታይነት ያለው ልብ ወለድ እንደሆነ በማሰብ ልታነብብ አይገባም፡፡ ስለዚህ የምናነብበው ምን ዓይነት ስነ-ጽሁፍ እንደሆነ እና ያም ስነ-ጽሁፍ ምን ዓይነት ቅንብሮችን እንዳዘለ ልንረዳ ይገባናል፡፡ [ዶ/ር ሪቻርድ ቡክሃም]***

የወንጌላትን ስነ-ጽሁፋዊ ባህርይ ከሁለት አተያዮች አንፃር እንዳስሳለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የወንጌላትን አይነት እንመረምራለን፣ ያም ማለት ሁሉን ጠቅልሎ የሚይዘውን ስነ-ጽሁፋዊ ባህርቸውን ማለት ነው፡፡ ሁለተኛ፣ ታሪካዊ ተዓማኒነታቸውን እንመረምራለን፡፡ አስቀድመን የአራቱን ወንጌላት ዐይነት እንመረምራለን፡፡

# ዐይነት (ዣንራ)

በጥቅል አነጋገር፣ ዐይነት የአንድ ስነ-ጽሁፍ ጎራ ወይንም ዐይነት ማለት ነው፡፡ ዐይነቶች (ዣንራዎች) አንዳቸው ከሌላቸው የሚለዩት በስነ-ጽሁፋዊ ቅርፃቸው ወይንም ተግባራቸው ማለትም፣ በአተራራክ ዘይቤያቸው እና በተምሳሊታዊ ቋንቋ አገባባቸው ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በርካታ ዐይነቶችን ያዘለ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በብሉይ ኪዳን ስነ ዳዊት የተነገሩ ታሪኮችን የያዙ ታሪካዊ ትረካዎች አሉ፡፡ ሌላኛው ዓይነት ደግሞ እንደ መዝሙረ ዳዊት የመሳሰሉትን የሚያካትተው ግጥም ነው፡፡ ደብዳቤዎች ወይንም መልዕክቶች ደግሞ ሌላዎቹ ሲሆኑ፣ ትንቢትና ሌሎችም አሉበት፡፡ እያንዳንዱ ዓይነት መልዕክቱን የሚስተላልፍበት የራሱ መንገድ አለው፡፡ የወንጌላትን ዓይነት መረዳታችን ወሳኝ የሚሆነው ለዚህ ነው፡፡ አስቀድመን እንዴት ትምህርታቸውን እንደሚያስተላልፉ ከተረዳን፣ ምን እንደሚያስተምሩ መረዳቱ ይቀለናል፡፡

ወንጌላት እንዴት መልዕክታቸውን እንደሚያስተላልፉ ለመረዳት፣ ዓይነቶቻቸውን በሦስት ደረጃዎች ከፋፍለን እናብራራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ወንጌላት እንደተሪካዊ ትረካ የሚገልጥልንን ጥቅል መግለጫ እናስቀምጣለን፡፡ ሁለተኛ፣ ግሪኮ-ሮማዊ ከሆነው ታሪካዊ በሰዎች የሕይወት ታሪክ ላይ ከሚጠነጥነው ታሪካዊ ትረካ ጋር እናነፃፅራቸዋለን፡፡ ሦስተኛ፣ ወንጌላትን በብሉይ ኪዳን ከተመዘገቡት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች ጋር እናስተያያቸዋለን፡፡ እስኪ አስቀድመን ጥቅል በሆነው ታሪካዊ ትረካ እንጀምር፡፡

## ታሪካዊ ትረካ

ታሪካዊ ትረካዎች በቀደመው ዘመን ስለነበሩ ሰዎች የሚወሱ ሲሆን በእነርሱ ዘመን ስለተከናወኑ ክንውኖችና ሁነቶች ይዘግባሉ፡፡ በመሠረታዊ ደረጃ፣ ወንጌላት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት የሚዘግቡ በመሆናቸው ታሪካዊ ትረካዎች ናቸው፡፡

> ***እኛ ታሪክ ወዳድ ሕዝቦች ከመሆናችን የተነሳ፣ አብዛኛዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችና ወንጌላት ራሳቸው በዓላማ በትረካዊ ቅርጽ እንዲፃፉ ተደርጓል፡፡ አንድን አስደናቂ ታሪክ በምናነብበት ወቅት፣ ያለምንም ውጫዊ ግፊት በቀላ እንማረካለን፣ ያም በአዕምሯችን ብቻ ሳይሆን በስሜቶቻችንና በመላ አካላችንም ጭምር እንመሰጣለን፡፡ ታሪኮች በተጨማሪም***

*በሌሎች ሰዎች የሕይወት ተሞክሮ ኑሯችንን እንድናቀና ያግዙናል፡፡ ይህ እንግዲህ የታሪክ ኃይለኛ ጎኑ ነው፡፡ ስለዚህም ወንጌላት ለእኛ የደረሱት በትረካዊ ስነ-ጽሑፍ ቅርፅ በመሆኑ፣ ስለ ኢየሱስ የተነገሩትን እውነቶች እንድናውቅ ብቻ ሳይሆን፣ እርሱን ልክ በአካል እንዳገኘ ሰው እንድንረዳው፣ የእግዚአብሔርንም መንግሥት በተግባር በመካከላችን እንዳለች እንድንረዳ፣ ኢየሱስ ትሁታንን ይወድዳል የሚለውን አባባል ብቻ ሳይሆን፣ ርኅራኄውን እንድናይ ማለትም ታሪኮችን ሲናገር እና የተናገረውንም ትሑታን ከፍ በማድረግ ትዕቢተኞችንም በማዋረድ በተግባር ሲያሳየን እንመለከተዋለን፡፡ በወንጌላት ውስጥ የምናገኛቸው ታሪኮችና ስነ-ጽሁፋዊ ቅርፆች ልክ ደቀመዛሙርቱ ያደርጉ እንደነበረው የኢየሱስን ፈለግ እንድንከተል ያስችሉናል፡፡ ታሪኮችን በትረካ መልክ ማግኘታችን ኢየሱስን በዚያን ዓይነት መንገድ እንድንከተል ያስችሉናል፡፡ በተጨማሪም ራሳችን ከገጸባህርያቱ ውድቀትና ስኬት ጋር እንድናስተያይ እና የግል ሕይወታችንንም በታማኝነት እንድንመራ ያግዙናል፡፡ [ዶ/ር ጆናታን ፔኒንግተን]*

በጥንታዊው ዓለም ዓለማዊ ጽሑፎች ውስጥ፣ ታሪካዊ ትረካዎች በዋናነት በሦስት ክፍሎች ይዋቀራሉ፡፡ የትረካው መጀመሪያ የገጸባሕርዩን ማንነትና እንዲያሳካ የሚጠበቅበትን ግብ ያስተዋውቀናል፡፡ በመካከሉ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ገጸባሕርዩ የሚጠበቅበትንግብ ለማሳካት በሚያደርገው እንቅስቃሴ የሚገጥሙትን እንቅፋቶች ያሳየናል፡፡ መደምደሚያው ደግሞ የክስተቶቹን ማጠቃለያ ያቀርብልናል፡፡ አብዛኛወን ጊዜ ገጸባሕርያቱ ግባቸውን ማሳካታቸውን ወይም አለማሳካታቸውን ያመለክቱናል፡፡

ወንጌላትም ይህንኑ መሠረታዊ አስተዋፅዖ ይከተላሉ፡፡ እያንዳንዳቸውም ኢየሱስን የታሪኩ ዋነኛ ገፀ-ባህርይ እንደሆነና ግቡም በእግዚአብሔርም መንግሥት አማካይነት ድነትን ማምጣት እንደሆነ በማስተዋወቅ ይጀምራሉ፡፡ ሁሉም የኢየሱስ ሥልጣንና ሥራ የገጠመውን ተግዳሮት በማቅረብ ቀጣዩን ያመለክታሉ፡፡ ሁሉም ደግሞ በኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት ስለተገኙ ውጤቶች በመናገር ይደመድማሉ፡፡ በነዚህ መመሳሰሎች ምክንያት፣ ታሪካዊ ትረካ የወንጌላት አብይ የስነ-ጽሑፍ ዓይነት መሆኑን አብዛኛው ሰው ይስማማል፡፡

# ግሪኮ-ሮማዊ የሕይወት ታሪክ

አንዳንድ ተርጓሚዎች ወንጌላት በትልቁ ታሪካዊ ትረካ ውስጥ የግሪኮ-ሮማዊውን የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ ዘዴ ይከተላሉ የሚለውን ሃሳብ ያቀርባሉ፡፡

በወንጌላትና በግሪኮ-ሮማዊው የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ ዘዴ መካከል ያለውን ንፅፅር በሁለት ደረጃዎች እንመለከተዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ በመካከላቸው ያለውን ተመሳሳይነት እናያለን፡፡ ሁለተኛ፣ ያሏቸውን ጥቂት ልዩነቶች እንመለከታለን፡፡ በተመሳሳይነታቸው እንጀምር፡፡

***ተመሳሳይነታቸው፡*** ጥንታውያኑ የሕይወት ታሪኮች የታላላቅ መሪዎችን ሕይወት መልሰው ያሳዩናል፡፡ ምንም እንኳን የተለያዩ ገፀባሕርያትንና ታሪኮችን ቢያካትም፣ ግሪኮ-ሮማውያኑ የሕይወት ታሪክ አጻጻፎች እነዚያ ገፀባሕርያትና ታሪኮች ዋነኛውን ገፀባሕርይ እንዲያጎሉ አድርገው

ያስቀምጧቸዋል፡፡ የመሪውን ሃሳብ ይሚገቱለታል፣ ደግሞም ያከናወናቸው ተግባራት ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ያደርጋሉ፡፡ ወንጌላትም በነዚህ መንገዶች ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

በተጨማሪም የማቴዎስና የማርቆስ ወንጌላት የኢየሱስን የውልደት ታሪክ ያካተቱ ሲሆን፣ አራቱም በኢየሱስ ሞት ዙሪያ ዝርዝር ማቅረባቸውን ስንመለከት፣ ከጥንት የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ ጋር ያላቸውን ተጓዳኝነት እናያለን፡፡ ወንጌላት በተጨማሪም በኢየሱስ ሕይወት በተከናወኑ ድርጊቶች ላይ ስለሚያተኩሩ የጥንት የሕይወት ታሪክ አፃፃፍን ስምምነት ይከተላሉ፡፡ ልክ እንደሌሎቹ ጥንታውያን የሕይወት ታሪክ አፃፃፎች ሁሉ ወንጌላትም በኢየሱስ ውልደትና ሞት መካከል የተከናወኑ ድርጊቶችን በየፈርጁ ያሰልፋሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜም ነገሮችን በጊዜ ቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ፡፡በሌላ ጊዜ ደግሞ ነገሮችን በርዕስ በርዕስ ይመድባሉ፡፡  አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በመልከዓ ምድራዊ አቀማመጥም ያስቀምጣሉ፡፡

> ***እንደማሰበው አስቀድመን፣ ወንጌላት በጥቅሉ ቅደም ተከተልን የሚጠብቁ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ፣ በመጥምቁ ዮሐንስ የጥምቀት አገልግሎት ይጀምሩና ፣ የኢየሱስን መጠመቅ ያስከትላ፣ ከዚያም የኢየሱስን አገልግሎት ታገኛላችሁ፣ ያ ደግሞ መያዙን፣ መከራውን፣ መሰቀሉንና ትንሣኤውን ያስከትላል፡፡ ጠቅለል ስናደርገውም፣ ትርጉም ያለው ቅደም ተከተል መኖሩን ታያላችሁ፡፡ እንደዚያውም ደግሞ፣ ሁለት ወንጌላትን በምታስተያዩበት ወቅት፣ ስፍራዎችን ታገኛላችሁ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ክስተቶችን ታገኛላችሁ ወይም ለየት ባለ ቅደም ተከተል የተቀመጡ ንግሮችንም ጣገኛላችሁ፡፡ ችግር ውስጥ የምንገባው፣ በጣም ጥቃቅን በሆኑት ጉዳዮች እንኳን ሳይቀር፣ ወንጌላት ዝንፍ የማይል ቅደም ተከተል አላቸው ብለን ለመሟገት ካሰብን ነው፡፡ ግን አብዛኞቹ ፀሐፍት እና አብዛኞቹ ትረካዎች ፀሐፊው ሁሉን በቅደም ተከተል የማስፈር ግዴታ ውስጥ ሳይገባ ታሪኩን እንዲያዋቅር ይፈቅዱለታል፡፡ ለምሳሌ፣ አብዛኛውን ጊዜ ትርጉም የሚሰጥን ፍሰት ወይም ነገረ ጉዳዮችን በርዕስ በርዕሳቸው ማቧደንን ሊከተሉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ቀደምት ከሆኑት ክርስቲያኖች አንዱ የሆነውና የአራተኛው ክፍለ ዘመን ክርስቲያናዊ ታሪክ ፀሐፊ ጳጳሱ ኢዮሲበስ እንደጠቀሰው፣ በወንጌላት መካከል ያለው የቅደም ተከተል ልዩነት በስፋት ይታወቃል፣ ሆኖም ግን ለቀደምቱ አንባቢዎች ጉዳዩ ችግር አልነበረም ምክንያቱም የከረረ ቅደም ተከተልን ሊጠብቅ ይገባዋል ብለው አይጠብቁም ነበርና ነው፡፡ [ዶ/ር ዴቪድ ሬደሊንግስ]***

ሌላኛውና እጅግ ወሳኝ የሆነው ግሪኮ-ሮማዊ የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ ባሕርይ ያለፉ ክስተቶችን ታሪካዊ እውነታዎች አድርጎ ማስቀመጡ ሲሆን ያም ማለት ያለፈው ነገር ከአሁኑ የተለየ ነው ማለት ነው፡፡  የሕይወት ታሪኮች በአንድ ወቅት በነበሩ ታሪካዊ ግለሰቦች የተለየ እና ሊደገም የማይችል አስተዋፅዖዎቻቸው ላይ ያተኮሩ ዘገባዎችን ያቀርባሉ፡፡

በጥቅሉ፣ ጥንታዊ የሕይወት ታሪኮች በቃል ወይንም በጽሑፍ የተቀመጡ ታሪኮችን በትክክል በመመርመሩና በመጠበቁ ላይ ያተኩራሉ፡፡ ለምሳሌ ከ46 እስከ 120 ዓ.ም. የኖረውን ታዋቂ በሆነው የታሪክ ፀሐፊ ፕሉታርክ የተናገረውን  እንመልከት፡፡ ፕሉታርክ ግሪካዊ የታሪክ ፀሐፊ ሲሆን ፅሑፉን የጻፈውም ወንጌላት በተፃፉበት ተመሳሳይ ዘመን በ70 ዓ.ም. አካባቢ ነበር፡፡

ሥራውን የሚጀምረው ስለ ሲሴሮ ሕይወት ሲሆን ስለ ሲሴሮ ወላጆች ዳራ ሲጽፍ፣ ስለ ሲሴሮ አባት መረጃን የማግኘት ውሱንነት እንደነበረበት ተናግሯል፡፡

> ***ሄሊቪያ፣ የሲሴሮ እናት፣ በመልካም ሁኔታ የተወለደችና ጥሩ ሕይወት ትመራ የነበረች ሲሆን፤ ስለ አባቱ ግን በጣም የተራራቁ ነገሮችን ከማንሳት ባሻገር ምንም የተባለ ነገር የለም፡፡ ለምሳሌ አንዳንዶች የፉለር ልጅ፣ ስለ ንግድም የተማረ ነበር ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ የቤተሰቡን ግንድ ወደ ኋላ በመመለስ በሮማውያን ላይ በከፈተው ጦርነት ሁሉ ድል ሳይቀናው ቀርቶ የማያውቀው የቮልካኖች ንጉሥ ዕውቁ ቱለስ አቲየስ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡***

የሲሴሮን ወላጆች አስመልክቶ ፐሉታርክ የሰጠው ማሳሰቢያ የሚያመለክተን ቢያንስ አንዳንዶቹ ጥንታዊ የሕይወት ታሪክ ጸሐፍት ለታሪካዊ ዝርዝር ጉዳዮች ልዩ ትኩረት ይሰጡ እንደነበረና ሁሉን በጥንቃቄ ያለ አንዳች እንከን ለማስፈር መሻቱ እንደነበራቸው ያመለክታል፡፡ ወንጌላትም ልክ ፐሉታርክ እንዳደረገው በዘገባዎቻቸው ለጥቃቅኗ ነገር ሁሉ ጥንቃቄ የተሞላበት ማስረጃ አቅርበዋል፡፡

ሰፋ ባለ ሁኔታ ስንመለከተው፣ ወንጌላት በግሪኮ ሮማዊው ዓለም የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ ዕውቅ በነበረበት ዘመን የተጻፈ ታሪካዊ ትረካ እንደሆነ መናገሩ አግባብነት ይኖረዋል፡፡ ይህ ለሕይወት ታሪክ ሰፊ ስፍራ የመስጠቱ ነገር የወንጌላትን ጸሐፍት ያበረታታቸው ይመስላል፣ ደግሞም የነዚህን የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ ስምምነቶች እነርሱም ወደመጠቀሙ እንዲያዘነብሉ አድርገዋቸዋል፡፡

ነገር ግን በወንጌላትና በግሪኮ ሮማዊው የሕይወት ታሪክ አጻጻፎች መካከል ተመሳሳይነት የመኖሩ ነገር እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩነቶችም አሏቸው፡፡

**ልዩነቶች፡** ልንጠቅስ የምንችላቸው በርካታ ልዩነቶች ቢኖሩም፣ በሦስቱ ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ወንጌላት ታስቦበት ከተጻፈላቸው ተደራሲያን አንጻር ከግሪኮ ሮማዊው የሕይወት ታሪክ የተለዩ ናቸው፡፡

ጥንታዊ የሕይወት ታሪኮች ተደራሲያኖቻቸው ሰፊ ሲሆኑ፣ ወንጌላት ግን በጥንቲቷ ቤተክርስቲያን ለነበሩ ክርስቲያኖች የተጻፉ ነበሩ፡፡ ምንም እንኳን አንዳንድ የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ ባሕርያት ቢታዩባቸውም፣ በመሠረታዊ ረገድ ግን የተጻፉት በቤተክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት ላይ ለሚውሉ ሃይማኖታዊ ጠቀሜታዎች ነበር፡፡ ይህ የተለየ ንድፍ እውን መሆኑ የተረጋገጠው በቤተክርስቲያን የአምልኮና የትምህርት ፕሮግራሞች ላይ በፍጥነት አገልግሎት ላይ ውለው በመገኘታቸው ነው፡፡

ሁለተኛ፣ ወንጌላት በሚሰጡት አፅንዖት ከሌሎቹ የሕይወት ታሪኮች ይለያሉ፡፡ ግሪኮ ሮማዊው የሕይወት ታሪክ አፅንዖት የሚሰጡት ለዋና ገፀ ባሕርቶቻቸው ምርጥ ስብዕና ሲሆን፣ ተደራሲያኑም እነዚያን ድንቅ ባሕርያት እና የሕይወት ዘይቤ እንዲቀዱዋቸው ያበረታታሉ፡፡ ምንም እንኳን የኢየሱስ ሕይወት በብዙ ረገድ ምሳሌያችን የሚሆንባቸው መንገዶች ቢኖሩም፣ ወንጌላት ግን ለየት ያለ ትኩረት አላቸው፡፡ ኢየሱስ አምሳያ የለሽ በመሆኑ ላይ አፅንዖት ይሰጣሉ፡፡ እርሱ እግዚአብሔርን የገለጠልንና ሕዝቡንም የተቤዣ አምሳያ የሌለው በመሆኑ ላይ ያተኩራሉ፡፡

የወንጌላቱ ዐቢይ ትኩረት በእርሱ ሕይወት የመጨረሻ ሳምንት ላይ የሆነው ከዚህ የተነሳ ነው፡፡ ይህ ሳምንት የህማማት ሳምንት ነው፡፡

ሦስተኛ፣ ወንጌላትና ቀደምት የሕይወት ታሪኮች የሚወክሉት የተለያዩ ባህሎችን ነው፡፡ የሕይወት ታሪኮቹ የግሪኮ-ሮማዊውን ፍላጎቶች፣ እሴቶችና የሕይወት ዘይቤዎች መግለጫ ይሰጣሉ፡፡ ወንጌላት ደግሞ የአይሁድ ወጎች በተለይም የብሉይ ኪዳን ጫና የሚያርፍባቸው ናቸው፡፡ ይህም የግሪክ ባህልና አስተሳሰብ ጫና አሳድሮበታል በምንለው በሉቃስ ወንጌል ላይ እንኳን እውነትነት አለው፡፡

ስናጠቃልለው፣ በወንጌላትና በግሪኮ-ሮማዊው የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ ውስጥ ሊጠቀስ የሚችል ተመሳሳይነት አለ፡፡ እነዚህም መመሳሰሎች በወንጌላት ፍቺ ላይ የራሳቸውን ብርሃን ይፈነጥቃሉ፡፡ በመካከላቸው ካለወ ልዩነት አንፃር ግን፣ ወንጌላት ከግሪኮ-ሮማዊው የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ ጋር ፍፁም ግጥምጥም የሚሉ አለመሆናቸው ግልፅ ነው፡፡

ወንጌላትን ከአጠቃላዩ ታሪካዊ ትረካና ከግሪኮ-ሮማዊው የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ ጋር ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪካዊ ትረካዎች ጋር እናስተያያቸዋለን፡፡

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪካዊ ትረካዎች

ወንጌላት ከአጠቃላዩ ታሪካዊ ትረካና ከግሪኮ- ሮማዊው የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ ጋር ተመሳሳይ የሆኑትን ያህል፣ ከብሉይ ኪዳኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪካዊ ትረካም ጋር በእጅጉ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ይህም ሊያስደንቀን አይገባም፡፡ የብሉይ ኪዳን ታሪኮች የወንጌላት ፀሐፍት እዚህም እዚያም ይጠቅሷቸው የነበሩ ቅዱስ መጻሕፍቶቻቸው ነበሩ፡፡ እያንዳንዱ የወንጌል ጸሐፊ የጠቀሳቸውን የብሉይ ኪዳን ማጣቀሻዎች ስንመለከት፣ የዛሬው ክርስቲያን ከሚያውቀው የበለጠ ብሉይ ኪዳንን ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ ከብሉይ ኪዳን ጋር የነበራቸው ቀረቤታ ሥራቸውን እንዴት እንደሚጀምሩት የራሱን ጫና አሳድሮባቸዋል፡፡

ከዚያም ባሻገር፣ የወንጌላት ፀሐፍትና የብሉይ ኪዳን ታሪካዊ ትረካ ፀሐፊዎች የፃፉት በተመሳሳይ ዓላማ ሲሆን ይህም እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ለገባው ቃል ኪዳን ተሟ ጋች መሆን ነው፡፡ ለአብነት ያህል፣ በዘፀአት ምዕራፍ 1 እስከ 19 ያሉት ታሪኮች በዘፀአት 20 እስከ 24 ላለው ሙሴያዊ ኪዳን ታሪካዊ መሠረቶች ናቸው፡፡

ይህ ዓላማ በዘፀአት ምዕራፍ 24፥8 በመሳሰሉት ምንባቦች በግልፅ ተቀምጧል፡፡

> *ሙሴም ደሙን ውሰዶ በሕዝቡ ላይ ረጨው። በዚህ ቃል ሁሉ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያደረገው የቃል ኪዳኑ ደም እነሆ አለ። (ዘፀአት 24፥8)*

ለምሳሌ እንደ ኢያሱ ምዕራፍ 1 እስከ 23 ያሉት ሌሎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች፣ በኢያሱ ምዕራፍ 24 ላለው የቃል ኪዳን ኅዳሴ መሠረቶች ናቸው፡፡ ደግሞም በመሳፍንትና በ1ኛ ሳሙኤል መጻሕፍት ያሉት ታሪኮች ደግሞ በ2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 7 ለምናገኘው ዳዊታዊ ቃል ኪዳን

ታሪካዊ መሠረቶች ናቸው፡፡ በተመሳሳይም መንገድ፣ ወንጌላትም በኢየሱስ ለተመሠረተው አዲስ ኪዳን ታሪካዊ መሠረቶች ናቸው፡፡

እስኪ በሉቃስ 22፥20 የተፃፈው ታሪክ በዘፀአት 24፥8 የተፃፈውን እንዴት እንደሚያስተጋባ እንመልከት፡-

> *እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ፡- ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው። (ሉቃስ 22፥20)*

ስናጠቃልለው፣ ወንጌላትን ከሌሎች ዕውቅ ስነጽሁፋዊ ዐይነቶች ጋር ስናነፃፅራቸው፣ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች ጋር በእጅጉ ተመሳሳይነት ያላቸው ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ይህ ማለት ግን በሁሉም ረገድ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች ጋር ፍፁም አንድ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ ከግሪኮ-ሮማዊው የሕይወት ታሪክ አፃፃፍም አንዳንድ ገፅታዎችን ተውሰዋል፡፡ በዚህ ረገድ፣ ወንጌላት የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትሪክ አዲስ የአፃፃፍ ዓይነቶች ናቸው ማለት እንችላለን፡፡ ስለዚህ፣ ስናነባቸው፣ በተቀዳሚነት ወንጌላት የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪካዊ ትረካ አካል መሆናቸውን ማሰብ ተገቢ ነው፡፡ ከዚያም በሻገር ደግሞ በኢየሱስ የሕይወት ታሪክ ላይ የሰጡትንም አፅንዖት ልብ በማለት ሌሎቹን ባሕርያቶቻቸውን ከእርሱ ጋር በተገናኘ መንገድ ልንፈታ ይገባናል፡፡

የወንጌላትን ዓይነት ከተመለከትን፣ ወንጌላት ስለ ኢየሱስ ሕይወት የሚተርኩ ወደ መሆናቸው የተዓማኒነት ጥያቄ እንሸጋገራለን፡፡

# ተዓማኒነት

በየታሪክ ዘመናቱ፣ ተዓማኒ በሆኑትና ባልሆኑት የታሪክ ፀሐፍት መካከል፣ ተዓማኒ በሆኑትና ባልሆኑት ምንጮች መካከል ልዩነቶች ሲንፀባረቁ ኖረዋል፡፡ አሁን እኛን የሚጠብቀን ጥያቄ፡ የአራቱ ወንጌላት ፀሐፍት ስለ ኢየሱስ ሕይወት የፃፉት ተዓማኒ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡ በእኛ ዘመን ያለን መመዘኛ እነርሱ ከተከተሉት የሚለይ ቢሆንም፣ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ለመጻፍ ተዓማኒነት ያለው ምንጭ እንደነበራቸውና ተነሳስቶአቸውም ጤነኛ እንደሆነ የሚስረዳ በቂ መረጃ አለ፡፡

ምንም እንኳን ወንጌላት ተዓማኒ የሆኑ ታሪካዊ ማስረጃዎች መሆናቸውን የምናረጋግጥባቸው ከቁጥር በላይ የሆኑ መንገዶች ቢኖሩም፣ በስድስቱ ማስረጃዎች ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡

## መረጃን የማግኘት እድል

በመጀመሪያ፣ የወንጌላት ፀሐፍት ስለዘገቧቸው ክስተቶች በቂ መረጃ የማግኘት እድል አላቸው፡፡ ልክ እንደዛሬው ሁሉ፣ ጥንታዊውም ዓለም ተዓማኒ ፀሐፊዎች ለሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ የሚጠቅሙ እውነታዎች መረጃ እንዲኖራቸው ይጠብቅባቸዋል፡፡

አንድ ጊዜ መለስ ብለን ሮማዊውን ታሪክ ፀሐፊ ፕሉታርክን እንመልከተው፡፡ በዲሞስቴነስ ሕይወት ላይ በፃፈው መግቢያ ላይ፣ አንድ ታሪክ ፀሐፊ የሚጠበቅበትን ባህላዊ ጥበቃ አስመልክቶ እነዚህኑ መሠረታዊ ነገሮች አስፍሯል፡፡

***አንድ ሰው ታሪክ መፃፍ ሲፈልግ... ከሁሉ አስቀድሞ እና ከሁሉም በላይ ከሁሉም ዘርፍ የተለያዩ መፃሕፍትን ሊያገኝ ይገባል፣ ... ስለ እያንዳንዳቸውም ጉዳዮች መረጃው ሊኖረው፣ ከፀሐፊ ብዕሮች ያመለጡትን ደግሞም በሰዎች አዕምሮ በታማኝነት የተቀመጡትን በመስማት ሊያረጋግጥ ይገባል፣ ይህንን ካላደረገ ሥራው በብዙ መንገዶች እንከን ያለው ይሆናል፡፡***

በዚህ ስፍራ እንዳየነው፣ አንድ የታመነ ታሪክ ፀሐፊ ለታመኑ ምንጮች ቅርበት ያለው ሊሆን የሚገባ መሆኑን ፕሉታርክ በብርቱ ያምናል፡፡ በተቻለ መጠን ሊገኙ ለሚችሉ ምንጮች ማለትም የተፃፉም ሆነ በቃል ሲተላለፉ የኖሩትን በጥንቃቄ የመመርመርን አስፈላጊነት አፅንዖት ሰጥቶታል፡፡

የወንጌላት ፀሐፊዎችም አንድም ለኢየሱስ ሕይወት ራሳቸው የዐይን ምስክሮች ናቸው አሊያም ለኢየሱስ ሕይወት የዐይን ምስክሮች ከሆኑት ጋር የቀጥታ ግንኙነት አላቸው፡፡ ማቴዎስና ዮሐንስ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት እስከሆኑ ድረስ፣ የዘገቡት በስፍራው ኖረው ያዩትን ነው፡፡ ማርቆስ ደግሞ የጴጥሮስ የቅርብ ባልደረባ የነበረ ሲሆን፣ ከእርሱ በቀጥታ መረጃውን አግኝቷል፡፡ ሉቃስ ደግሞ ከጳውሎስ ጋር ይጓዝ የነበረ ሲሆን ለወንጌሉ ጠቃሚ መረጃ የሚሰጡትን የዐይን ምስክሮች የማግኘት እድል ነበረው፡፡ በሉቃስ 1፥1-3 የፃፈውን አድምጡ፡-

የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ፥ ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፥ በኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ፥ እኔ ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ። (ሉቃስ 1፥1-3)

## ግልጽነት

ሁለተኛ፣ የወንጌላትን ታሪካዊ ተዓማኒነት በከፍተኛ ግልጽነት ደረጃ ተመልክተነዋል፡፡ ጥንታዊው የመልካም ታሪክ አፃፃፍ ስታንዳርድ እንደሚነግረን ታሪክ ፀሐፊዎች በፅሁፋቸው ግልፅ፣ቅንና እውነተኛ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ በሚተላለፈው መልዕክት ውስጥ አሳፋሪ የሆኑትን ጨምሮ መጠነ ሰፊ መግለጫ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በዚህ ረገድ፣ የወንጌላት ፀሐፊዎች የኢየሱስን ደቀ መዛሙርት ውድቀቶች ደግመው ደጋግመው መግለጣቸው ወሳኝነት አለው፡፡ ማቴዎስና ዮሐንስ የራሳቸውን ድክመት መግለጣቸው የዚህን ፍቺ እውነትነት ይገልጥልናል፡፡ አንዳንድ ተርጓሚዎች እንደሚገልፁት በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 14፥51-52 ከጌተሰማኒ የአትክልት ስፍራ ራቁቱን የሸሸው ወጣት ማርቆስ ከሆነ፣ ማርቆስ ራሱ ድክመቱን ዘግቧል ማለት ነው፡፡ ያለምንም ልዩነት፣ ሁሉም የወንጌላት ፀሐፊዎች የኢየሱስን

ደቀመዛሙርት ድክመቶች አጋልጠዋል፣ ያንንም ያደረጉት ገና ታዳጊ የነበረችው ቤተክርስቲያናቸው መሪዎች እንቅስቃሴ ፍፁምነት ያልነበረው መሆኑን ለማመልከት ነበር፡፡

አንድ ምሳሌ ለመውሰድ ያህል፣ በማርቆስ 6፥51-52 ኢየሱስ 5000ዎቹን መመገቡን የዘነጉበት የደቀመዛሙርቱ ድክመት ተመዝግቦልናል፡፡

> ወደ እነርሱም ወደ ታንኳይቱ ገባ፥ ነፋሱም ተወ፤ በራሳቸውም ያለ መጠን እጅግ ተገረሙ፤
>
> ስለ እንጀራው አላስተዋሉምና፤ ነገር ግን ልባቸው ደንዝዞ ነበር። (ማር 6፥51-52)

ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ የወንጌላት ፀሐፊዎች የኢየሱስን ደቀመዛሙርት አለመረዳቶችና ግብረገባዊ ድክመቶች መዝግበዋል፡፡ እነዚህን ውድቀቶች የመፃፉ ነገር የቤተክርስቲያንን መሪዎች ሥልጣንና ከበሬታ ለማቃለል ቢሆን ኖሮ፣ ለምን የወንጌል ፀሐፊዎች መዘገቡት?

> ***በወንጌላት ውስጥ ደቀመዛሙርቱ ፍፁምነት የጎደላቸውና መረዳታቸውም እንከን ያለበት መሆኑ የመመዝገቡ ነገር በርካታ አንባቢዎችን ግር ያሰኛቸዋል፡፡ ግን በእኔ አመለካከት፣ ይህ ነገር የሚያመለክተው የወንጌላትን ተውፊት ተዓማኒነት ነው፡፡ እንግዲያው ወንጌላውያኖቻችን የቀደሙት መሪዎች ምን ይመስሉ እንደነበር ክፉ የሆነ ነገር ባይኖር ቢያንስ በሁሉ አንከን አልባ እንዳልነበሩ ለመናገር ዝግጁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የእኛ ወንጌል ትክክለኛና አስተማማኝ የመሆኑ ምስክርነትም ይህ ነው፡፡ [ዶ/ር ዴቪድ ባወር]***
>
> ***በወንጌላት ውስጥ ደቀመዛሙርቱ በራሳቸው ታሪክ ውስጥ ድክመታቸውን ለመዘገብ መጨከናቸው የወንጌላት ሥልጣንና ተዓማኒነት ተሟጋች ከመሆን አንፃር ጠንካራው ማስረጃ ነው፡፡ ኢያችሁ፣ የጥንታውያኑን የባቢሎን ወይንም የአሦር ነገሥታትን፣ ወይም የሮምን ነገሥታት ታሪክ ስታነብቡ፣ ከድል ወደ ድል፣ ከአሸናፊነት ወደ አሸናፊነት የገሠገሡበትንና "ግርማዊ ብዝበዛዎቼ እነዚህ ናቸው" የሚል ታሪክ ብቻ ነው የምታገኙት፡፡ በእኛ ዘመን ግን መለስ ብለን ነገሩን ስናየው፣ በእውነት የሆነው ምን ይሆን? እንላለን፡፡ ደቀመዛሙርትን ስናያቸው ግን እንደተፃፈው ናቸው፡፡ እስኪ አስቡት ጀግናችን ነው ያሉት ሰው በሮማውያኑ በመንግሥት ላይ የማነሳሳትና የሕገወጥነት ማስረጃ ተደርጎ በተቆጠረበት፣ ለአይሁድ ደግሞ የመረገም ማረጋገጫ ተደርጎ በሚወሰድበት መንገድ በስቅላት የሞተበትን ሁኔታ የሃይማኖት መሠረት ማድረግ ምን ይሉት ይሆን? ይህ ነገር በእርግጥ የሆነ ካልሆነ ይህንን ይዞ የሚቆም ምንም አይኖርም፡፡ [ዶ/ር ዳን ዶሪያኒ]***

# ማረጋገጫ

ሦስተኛ፣ በወንጌላት ፀሐፊዎች ተዓማኒነት ላይ ያለን ሌላው እርግጠኝነት የሚጠናከረው ከሌሎች ታሪካዊ ምንጮች የምናገኘው ማረጋገጫ ነው፡፡ የሮማውያኑም ሆኑ የአይሁድ ታሪክ ፀሐፊዎች የወንጌላትን ዘገባ አረጋግጠዋል፡፡ ዘመናዊውም የቅሪተ አካላት ጥናት ዘገባቸው እውነት የመሆኑን ማስረጃ አግኝቷል፡፡

ለምሳሌ፣ ወጣቱ ፕሊኒ፣ ሱቶኒየስ፣ታሲተስ እና ጁሊየስ አፍሪካኑስ የተሰኙት ግሪኮ ሮማውያኑ የታሪክ ፀሐፍት ስለ ኢየሱስ ሕይወት ማለትም በስቅላት ስለ መሞቱ እና ለዘመናት ስለዘለቀው ተፅዕኖው ጠቅሰዋል፡፡

*ኢየሱስ ክርስቶስ ነዋሪና በርካታ ተከታዮች እንደነበሩት የጠቀሰልንን በመጀመሪያው ዓመተ ምህረት የአይሁዳውያንን ታሪክ ለሮማውያኑ የዘገበውን አይሁዳዊውን ታሪክ ፀሐፊ የሲፈስን እናገኛለን፡፡ ሌላው ደግሞ የሲፈስ በኖረበት ተመሳሳይ ዘመን የኖረው ሮማዊው ታሪክ ፀሐፊ ታሲተስ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን በርካታ ተከታዮች የነበሩት ሲል ጠቅሶታል፡፡ የአይሁዳውያኑ ታልሙድም ኢየሱስ የነበረ እንደሆነ ጠቅሶታል፡፡ [ዶ/ር ስቲቨን ሶካላስ]*

*እኔ እንደማስበው በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ስለነበረችው የፓለስታይኗ የአይሁድ ምድር ከዛሬ ሃምሳ ዓመታት በፊት ከነበረን ግንዛቤ እጅግ በላቀ ደረጃ ላይ ስለምንገኝ፣ የወንጌላትን ተዓማኒነት ከማረጋገጡ አንፃር በአስተማማኝ ስፍራ ላይ ነን ማለት እችላለሁ፡፡ ይህንንም የምናውቀው የሙት ባሕር ጥቅልል ጽሑፎች ከመገኘታቸውና ከሌሎችም የቅሪተ አካላት ማስረጃዎች አንፃር ነው፡፡ በተጨማሪም፣ እስከ አሁን ድረስ በቅድስቲቱ ምድር አዳዲስ የቅሪተ አካላት ማስረጃዎች መገኘታቸው ቀጥሏል፡፡ ስለዚህም በኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን ስለተከናወኑት ተግባራት በርካታ ማረጋገጫዎችን እያገኘን ነው፡፡ እናም ወንጌላት የሚናገሯቸው ነገሮች ከአውዱ ጋር ተዓማኒነት ባለው መንገድ ይጣጣሙ ወይም አይጣጣሙ እንደሆነ በመጠየቅ የምናረጋግጥባቸው በርካታ መንገዶች አሉን፡፡ በአንድ ውሱን አውድ ስር ኢየሱስን እንደ አንድ የአይሁድ መምህር መቁጠር ትርጉም ይሰጣልን? እንደማስበውም፣ በጥቅሉ፣ ይህ ጉዳይ በትክክል የሚገጥም ነው ማለት እንችላለን፡፡ እንደምናስታውሰውም ከ66 እስከ 70 በተካሄደው የአይሁድ አብዮት በአይሁዷ ፓለስታይን ውስጥ ሁኔታዎች በፍጥነት ተቀያይረዋል፡፡ እንግዲያው ወንጌላት ከዚያ ዘመን ጋር የሚገጥም ነገር አላቸው ወይስ የሚዘግቡት ከአብዮቱ በኋላ ስላለው ነገር ነው የሚለውን ለማጣራት ጊዜው በጣም አጭር ነው፡፡ ሆኖም ልብ ልንለው የሚገባን ነገር ስለ መጀመሪያው ምዕተ ዓመት የአይሁድ ሃይማኖት የምናውቀው ነገር ከሁሉም ጽሑፎች ጋር ግጥምጥም ይላል ብለን መጠበቅ እንደሌለብን ነው፡፡ [ዶ/ር ሪቻርድ ቡክሃም]*

## ስልጠና

የወንጌላትን ዘገባ እንድናምን የሚያደርገን አራተኛው ምክንያት የኢየሱስ ደቀመዛሙርት የተቀበሉት ስልጠና ሲሆን ያም የእርሱን ቃላትና ሥራዎች በትክክል ያስተላለፉ ዘንድ የተማሩ መሆናቸው ነው፡፡

በአይሁድ ባህል ውስጥ፣ ደቀመዝሙርነት በውል የተደራጀ የሕይወት ዘይቤ ነው፡፡ በመሠረቱ፣ ለደቀመዝሙር አገልግሎት ላይ የዋለው የዕብራይስጡ ቃል ታልሚድ የሚል ሲሆን፣ ፍቺውም ተማሪ ማለት ነው፡፡ በተለይም፣ ደቀመዝሙር የአንድ እውቅ መምህር ተማሪ የሆነ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ በኢየሱስ ዘመን በነበረው የአይሁድ ባህል ውስጥ፣ ከአንድ ራቢ የመማሩ አንዱ ልምምድ የቃል ጥናት ነበር፡፡ እናም ከደቀመዛሙርቱ ሃላፊነቶች አንዱ ያስተማሪያቸውን ቃልና ጥበብ ማወቅ ነው፡፡ እስኪ ኢየሱስ በሉቃስ 6፥40 ለደቀመዛሙርቱ የተናገረውን አድምጡ፡

ደቀ መዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም፤ ፈጽሞ የተማረ ሁሉ ግን እንደ መምህሩ ይሆናል። (ሉቃስ 6፥40)

ኢየሱስ እያለ ያለው እርሱን የሚከተሉ ሁሉ የእርሱን ትምህርቶች ሊያጠኑ፣ ሊማሩና ሕይወታቸውንና ተግባራቸውንም በዚያው መሠረት ሊመሩ እንደሚገባ ነው፡፡

ዐሥራ ሁለቱ ከኢየሱስ ጋር ቅርበት የነበራቸው ደቀመዛሙርት የኢየሱስን ትምህርቶች ጠንቅቆ የመማር ሃላፊነቶች የነበረባቸው ቢሆንም፣ ከኢየሱስ ተምረው የነበሩትም በርካቶች ሰዎች የእርሱን ትምህርቶች በቃላቸው ያጠኑ ነበር፡፡

## ነገረ-መለኮታዊ ቁርጠኝነት

አምስተኛ፣ የወንጌላት ፀሐፊዎች እውነተኛና ተዓማኒነት ያለው ዘገባ የሚያስፈልግ የመሆኑ ነገረ-መለኮታዊ ቁርጠኝነት የነበራቸው መሆኑን ዝቅተኛ ግምት ልንሰጠው አይገባም፡፡ ለምሳሌ፣ በዮሐንስ 20፥31 ውስጥ ሐዋርያው ይህንን ጽፏል፡

ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል። (ዮሐንስ 20፥31)

በዚህ ምንባብ፣ እግዚአብሔር ለሕይወታቸው ያዘጋጀውን ስጦታ ሰዎች ሊቀበሉ የሚችሉት ስለ ኢየሱስ የተነገረውን እውነት ያወቁና የራሳቸው ያደረጉ እንደሆነ ብቻ መሆኑን ዮሐንስ ገልጧል፡፡

በተመሳሳይ መንገድ፣ ማቴዎስም በወንጌሉ በምዕራፍ 28፥19-20 ላይ እነዚህን የኢየሱስ ቃላት ዘግቧል፡

እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ። (ማቴ 28፥19-20)

በዚህ ስፍራ፣ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት እርሱ ያዘዛቸውን ሁሉ የማስተማር ሃላፊነት እንዳለባቸው ማቴዎስ ጠቅሷል፡፡ እንደ እውነተኛ የኢሱስ ተከታዮች፣ እርሱ ስላደረጋቸውንና ስለተናገራቸው ነገሮች ተገቢ መረጃ መስጠትን ቸል ሊሉት አይገባም፡፡

የወንጌላት ፀሐፊዎች በኢየሱስ ሕይወት የተከናወኑ ድርጊቶችን ለራሳቸው ታሪካዊ እሴት ሲሉ ብቻ አልመዘገቡም፡፡ በተቃራኒው፣ በኢየሱስ ማመን ስለ እርሱ ታሪካዊ ጭብጦችን ከማወቅ የዘለለ ነገር እንዳለው ተረድተዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር እውነተኛ እምነትም በተሳሳቱና በሚሻሩ መረጃዎችም

ላይ ሊመሠረት እንደማይችልም አውቀዋል፡፡ አንባቢዎቻቸው ታሪካዊውን ኢየሱስን እንዲያምኑት ስለፈለጉ፣ የኢየሱስን ንግግሮችና ተግባራት በግልፅነትና በትክክል ገልጠዋቸዋል፡፡

## መንፈስ ቅዱስ

ስድስተኛ፣ እንደ ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሐፍት፣ የወንጌላትም ፀሐፊዎች የኢየሱስን ቃሎችና ሥራዎች ሲጽፉ ለብቻቸው አልተተዉም፡፡ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ሥራቸው ውስጥ መርቷቸዋል፡፡

> ***የቅዱሳት መፃሕፍት በመንፈስ ቅዱስ መነዳት መጻፋቸው እጅግ ወሳኝ አስተምህሮ ነው ምክንያቱም ቅዱሳት መጻሕፍት አንድ ዋነኛ ደራሲ እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ ነው፡፡ እንግዲያው፣ ወንጌላትን ስንመለከትና ስለ ኢየሱስ አራት የተለያዩ አመለካከቶችን ያሰፈሩ አራት የተለያዩ ፀሐፊዎችን ስንመለከት፣ እነዚህ አመለካከቶች በመንፈስ ቅዱስ መነዳት የተገኙ መሆናቸውን እንደንገነዘብ ያደርጉናል፡፡ በነገረ-መለኮቱ እና በየፉላቸው ተደራሲያኖቻቸው፣ በዓራቸውና ከኢየሱስ ጋር በነበራቸው ልምምዶች ረገድ የተፃፉት በተለያዩ አጀንዳዎች ነው፡፡ ምንም እንኳን እንደ ሰብዓዊነታቸው የአፃፃፍ ልዩነቶች ቢኖሯቸውም፣ አስደናቂ አንድነትን እንመከትባቸዋለን፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መነዳት የመጻፋቸው ነገር ሰብዓዊውን እውነታ አላጠፋውም ወይም የሰዎችን ሥራ አላስወገደም፣ ይልቁኑ በእነዚህ ሰብዓዊ ፕረቶች ውስጥ እግዚአብሔር የሚፈልገውን በቀጥታ አከናወነበት፡፡ [ዶ/ር ኬ. ኤሪክ ቶኔስ]***

እስኪ ኢየሱስ በዮሐንስ 14፥25-26 የተናገረውን አድምጡ፡

> ከእናንተ ዘንድ ስኖር ይህን ነግሬአችኋለሁ፤
> አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል። (ዮሐ 14፥25-26)

የኢየሱስ ደቀመዛሙርት የቱንም ያህል ነገርን በቃል በማጥናቱ ረገድ የተዋጣላቸው ቢሆንም፣ ሁሉንም ነገር ልቅም ሊያደርጉት አይችሉም፡፡ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክ ተስፋ የሰጠውና የላከውም ለዚህ ነው፡፡ እናም መንፈስ ቅዱስ በየዘመናቱ የምትመጣው ቤተክርስቲያን ኢየሱስ የተናገራቸውንና ያከናወናቸውን ታውቅ ዘንድ ጠንቅቀው እንዲፅፉ አስችሏቸዋል፡፡ ዮሐንስ በወንጌሉ ምዕራፍ 21፥25 ላይ እንደ ፃፈው ማለት ነው፡፡

> ኢየሱስም ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ፤ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል። (ዮሐ 21፥25)

> ***ኢየሱስ ማን ነው የሚለውን ጥያቄ አንስተን ስንነጋገር እና ማንነቱን ስንጠይቃቸው፣ አንዳንድ ሰዎች ራቢ ነው፣ መምህር ነው፣ ይላሉ ወይም አንዳንዶቹ ደግሞ በዓለም ላይ እንዳሉት ሃይማኖቶች ዓይነት የሆነ የተለያየ ስም ይሰጡታል፡፡ ሆኖም በእግዚአብሔር ጥበብ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት፣ እግዚአብሔር የእርሱን የዐይን ምስክሮች በመምራት አራት ተመጋጋቢ የእምነት ቅርሶች እንዲፅፉልን አድርጓል፡፡ ስለዚህም በፀሐፊው በራሱም ይሁን***

*ምንጩ ባደረገው የዐይን ምስክርነት፣ቁርጥ ያለ ምስክርነትን ያኖረልን ሲሆን በመንፈስ ቅዱስም ከስህተት እንዲጠበቅ ያደረጋቸው በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስና በዮሐንስ ውስጥ የማረጋገጫ ልኬቶች ተቀምጠውልናል፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው **"ኢየሱስ እንዲህ ብሏል ወይም ኢየሱስ ይህንን ያደርጋል ወይም ያንን አያደርግም"** ብሎ ሲናገር፣ ፈጽሞ ሊካድ የማይቻል የተፃፈ እውነት ስላለን መለስ ብለን እናረጋግጣለን፣ ስለዚህም እግዚአብሔር እምነታችንን በፅኑ ዐለት ላይ አሳርፎልናል፡፡ [ዶ/ር ሮበርት ፕሉመር]*

# በቤተክርስቲያን ውስጥ ያላቸው ስፍራ

የወንጌላትን ስነ-ጽሁፋዊ ባሕርይ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደ ተፃፉ ሥልጣናዊ ምንባባት ያላቸውን ስፍራ እንመለከታለን፡፡ ወንጌላት በቤተክርስቲያን ውስጥ ያላቸውን ስፍራ በአፃፃፋቸውና በእግዚአብሔር ቃልነት ሥልጣናቸው አንፃር እንመረምራለን፡፡ አስቀድመን ስለ አፃፃፋቸው እንመልከት፡፡

## አፃፃፍ

ስለ ወንጌላት አፃፃፍ በምንነጋገርበት ወቅት፣ ወደ መፃፍ የመጡበትን መንገድ በልቡናችን ይዘን ነው፡፡ እነማን ፃፏቸው? ለምን ፃፏቸው? እንዴት ፃፏቸው? እነዚህን የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ለክርስቲያኖች በጣም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ከቁጥር በላይ የሆኑ ተርጓሚዎች የእነዚህን መጻሕፍት መለኮታዊ ሥልጣን ለማጥፋት በሰብዓዊ የአፃፃፍ ሂደት ላይ ብቻ ስለሚያተኩሩ ነው፡፡ የምሥራቹ ግን ጥንቃቄ የተሞላበት ምርመራ ካደረግን ወንጌላት የሰው ሥራዎች ብቻ ሳይሆኑ ቃለ እግዚአብሔርም ለመሆናቸው በርካታ ምክንያቶችን እናገኛለን፡፡

ከወንጌላት አፃፃፍ ጋር የሚዛመዱ ሦስት ጉዳዮችን እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ በተለያዩ ወንጌላት መካከል ያለውን ተመሳሳይነት እንዳስሳለን፡፡ ሁለተኛ፣ እነዚህን መመሳሰሎች የሚያብራሩ የአፃፃፍ ፅንሰ ሃሳቦችን እንዳስሳለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ለእነዚህ ፅንሰ ሃሳቦች ተገዢ ልንሆን የሚገባቸውንና እርግጠኛ የምንሆንባቸውን ሃሳቦችም እናቀርባለን፡፡ እስኪ በወንጌላት መካከል ባለው ተመሳሳይነት እንጀምር፡፡

## ተመሳሳይነት

ለየብቻቸው የተፃፉ ቢሆኑም፣ የማቴዎስ፣ የማርቆስ እና የሉቃስ ወንጌላት በአንድነት ተዋቅረው ተመሳሳዮቹ ወንጌላት (Synoptic Gospels) በመባል ይታወቃሉ፡፡ "Synoptic" የሚለው ቃል በቀላሉ በአንድነት የሚዩ የሚል ፍቺ ይይዛል፡፡ ወንጌላቱም ተመሳሳይ ማቴሪያል ስለሚጠቀሙ ስያሜው ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ተመሳሳይ የሆኑ የኢየሱስን ንግግሮችና ሥራዎች በብዛት ያካትታሉ፡፡ የኢየሱስን አባባሎች በሚጠቀሙ ወቅት፣ አንድ ዓይነት ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡

ለምሳሌ፣ ኢየሱስ ሽባውን የፈወሰበትን ሁኔታ ማንሳት ይቻላል፡፡ በማቴዎስ 9፥6 ውስጥ፣ እነዚህን የኢየሱስን ቃላትና ተግባራት እናነባለን፡

ነገር ግን በምድር ላይ ኃጢአትን ያስተሰርይ ዘንድ ለሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፥ በዚያን ጊዜ ሽባውን። ተነሣ፤ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው። (ማቴዎስ 9፥6)

የማርቆስን ደግሞ አድምምጡ፡

ነገር ግን ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ሊያስተሰርይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፤
ሽባውን። አንተን እልሃለሁ፥ ተነሣ፥ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው።
(ማርቆስ 2፥10-11)

በሉቃስ 5፥24 ደግሞ ይህንን እናነብባለን፡

ነገር ግን በምድር ላይ ኃጢአት ሊያስተሰርይ ለሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ ብሎ፥ ሽባውን። አንተን እልሃለሁ፥ ነተሣ፥ አልጋህን ተሸከመህ ወደ ቤትህ ሂድ አለው። (ሉቃስ 5፥24)

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ ኢየሱስ ያከናወነውን ተዓምራዊ ታሪክ ቃል በቃል ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ተመሳሳዮቹ ወንጌላት ማስፈራቸውን እናያለን፡፡ ከሦስቱ ተመሳሳይ ወንጌላት ቢያንስ በሁለቱ የሰፈሩ ሌሎች ተጓዳኝ ታሪኮችም አሉ፡፡ እነርሱም፡ የለምፃሙ መፈወስ፣ በቅፍርናሆም ኢጋንንትን ማስወጣቱ፣ የጴጥሮስ አማት መፈወሷ፣ ማዕበሉን ፀጥ ማድረጉ፣ የኢያኢሮስ ልጅ ከሞት መነሣቷ፣ ለዐሥራሁለቱ ሥልጣን መስጠቱ፣ ኢየሱስ በውሃ ላይ መራመዱ፣ እጁ የሰለለችው ሰው መፈወስ፣ በጥቂት እንጀራና አሣ አምስት ሺዎችን መመገቡ እና የኢሱስ በክብር መለወጥ ይጠቀሳሉ፡፡

***ሦስቱ፣ የማቴዎስ፣ የማርቆስና የሉቃስ ወንጌላት፣ በተደጋጋሚ ተመሳሳዮቹ ወንጌላት በመባል ይታወቃሉ ምክንያቱም ነገሮችን ይመለከቱ የነበሩት በተመሳሳይ መንገድ እንዲያውም በተመሳሳይ መነፅር የማየት ዓይነት ነበር፡፡ ያም ሁኔታ አንዳንድ ጊዜ ታዲያ አንዱ እየበቃ ለምን ሦስት አስፈለገን? የሚል ጥያቄ አዘል አግራሞት ይጭርብናል፡፡ ከነዚህ ከሦስቱ ተመሳሳይ ወንጌላት አንዱን ማጣት አሳዛኝ ይሆናል ምክንያቱም እያንዳንዳቸው በግል አንድ ለየት ያለ ነገር ያሳዩናልና፡፡ ስለዚህም በመካከላቸው ያሉትን መጠነኛ ልዩነቶች መመልከቱ መልካም ነው፡፡ የማርቆስ ወንጌል ከሌሎቹ ወንጌላት ይልቅ በአንዳንድ ግለሰባዊ ታሪኮች ላይ ዘርዘር ያለ ማብራሪያና ልዩ ልዩ ገፅታዎችን የሚያቀርብልን ወንጌል ነው፡፡ ምንም እንኳን አጭሩ ወንጌል ቢሆንም፣ ግለሰባዊ ታሪኮቹ ረዘም ባለ መጠን ተፅፈውበታል፡፡ ማቴዎስ ደግሞ እነዚያን ታሪኮች በጣም ያሳጠረና በሌሎች ነገሮች ላይ ማትኮር የፈለገ ወንጌል ነው፡፡ በተለይም ደግሞ፣ የማቴዎስ ወንጌል የማርቆስ ወንጌል እንግዳ በሆነ መንገድ የዘለላቸውን የኢየሱስን ትምህርቶች በዝርዝር ዘግቧል፡፡ ስለዚህ የማቴዎስ ወንጌል በሥልጣን ይነገሩ የነበሩ***

*የኢየሱስ ትምህርቶችን በመዘገብ መምህሩን ኢየሱስን ያሳየናል፡፡ ስለ ኢየሱስ ትምህርቶች ቅልጥፍ ያለ መረጃ ማግኘት የምንፈልግ ከሆነ የማቴዎስ ወንጌልን ማንበብ ተገቢ ነው፡፡ ሉቃስስ የሚያቀርብልን ምንድን ነው? ሉቃስ የሚያቀርብልን በአብዛኛው ትምህርቶችን ነው፡፡ ሉቃስ ደግሞ በአብዛኛው ምሳሌዎችን ያቀርብልናል ያም ከማቴዎስ ላቅ ባለ መንገድ ሲሆን ትኩረቶቹም ኢየሱስ ከሁሉም ዓይነት ሰዎች ጋር የነበረውን ቀረቤታ ማመልከትና ሰብአዊ ገፅታውን የሚያመለክቱ ሲሆኑ፣ ሁሉን የሚዳስስ፣ አፍቃሪና ስለ ሰው ግድ የሚለውን ኢየሱስን ያሳየናል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ሉቃስ ሐኪም ብቻ ሳይሆን፣ የስነ-አዕምሮ ጠቢብ ስነበር ሰብዓዊ ስሜቶችን በግሩም ሁኔታ ማስቀመጥ ችሏል ይላሉ፡፡ እናም እንደማስበው፣ በሦስቱም ወንጌላት ውስጥ፣ እጅግ ብርቅ የሆኑና ለእያንዳንዳቸው ዋጋ እብድንስጥ የሚያደርጉን የተለያዩ ምንባባትን እናገኛለን፡፡ [ዶ/ር ፒተር ዎከር]*

*ስለ ኢየሱስ ሕይወት ለመዘገብ ሦስት ወንጌላት ለምን አስፈለጉን ለሚለው ሃሳብ መሠረታዊ የሆነው ምክንያት ተዝቆ የማያልቀውንና ውብ የሆነውን የኢየሱስን ማንነት በአንድ መጽሐፍ ብቻ መገንዘብ ስለማይቻል ነው የሚለው ይሆናል፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር ልብ የነበረው ምን አንደነበረ ስናስብ፣ አንድ ፀሐፊ ብቻውን ኢየሱስ የፈፀመውን፣ የተናገረውንና ያደረጋቸውን ሁሉ አብጠርጥሮ ሊነግረን አይችልም፡፡ በዚህ ላይ ልጨምር የምፈልገው ነገር ቢኖር፣ በሦስቱ ወንጌላት መካከል ላሉትም ልዩነቶች ንቁ ልንሆን እንደሚገባን ነው፡፡ አዎን፣ በዋናነት የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ነው፣ ግን እያንዳንዳቸው በቀላሉ የማናያቸውን ግን ውብ የሆኑ ገፅታዎችን ለየብቻቸው ያቀርቡልናል፡፡ በአንድ ወገን ኢየሱስ ምን እንዳደረገ ምን እንደፈፀመ መሠረታዊ የሆነውን ታሪክ ሲነግሩን፣ በአንፃሩ ደግሞ ስለ ኢየሱስ የተለያዩ ገፅታዎችንም ያሳዩናል፡፡ እንግዲያው ነገሩ የብርቅርቅታ ዓይነት ነገር ነው፣ ሁሉም ነገር በዚያው ብርቅርቅታ ውስጥ አለ፣ ሆኖም ግን ከተለያዩ ጎኖች እናየዋለን እናም ስለ ኢየሱስ ማንነት የተለያ ምስሎች ይኖሩናል፡፡ በዚህም ስለ ኢየሱስ በርካታ ገፅጸዎችን የምናስተውልበትን የእግዚአብሔርን ጥበብና የመንፈስ ቅዱስን መግለጥ እናገኛለን፡፡ [ዶ/ር ቶማስ ሽሬነር]*

ከተመሳሳዮቹ ወንጌላት ጋር ስናነፃፀረው፣ የዮሐንስ ወንጌል በርካታ የራሱ መለያዎች አሉት፡፡ ዮሐንስም ኢየሱስ በውሃ ላይ መራመዱንና አምስት ሺዎቹን መመገቡን ቢዘግብም፣ በተመሳሳዮቹ ወንጌላት ያልተካተቱ በርካታ ክስተቶችን ግን ዘግቧል፡፡ ለምሳሌ፣ ኢየሱስ ወይኑን ወደ ውሃ መለወጡን፣ ከሳምራዊቷ ጋር ያደረገውን ንግግር እና አልዓዛርን ከሞት ማስነሳቱን ዘግቧል፡፡

ምንም እንኳን በአራቱም ወንጌላት ውስጥ የኢየሱስ አገልግሎትና ሕይወት በተለያ መንገድ ቢገለጥም፣ አራቱም ግን ስለ ኢየሱስ ጥምቀት፣ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ስለበላው የመጨረሻ እራት፣ በመስቀል ላይ ስለመሞቱና ከሞት ስለ መነሣቱ ግን አራቱም መስክረዋል፡፡

በወንጌላት መካከል ያሉት ስምምነቶችና ልዩነቶች አግባብነት ያለው መግለጫ ወደ መስጠቱ ያመራናል፡፡ እንግዲያው፣ እስኪ ስለ ወንጌላት አፃፃፍ ጽንሰ ሃሳብ እንነጋገር፡፡

## የአፃፃፍ ጽንሰ ሃሳብ

በተመሳሳዮቹ ወንጌላት መካከል ካሉት ተመሳሳይ ነገሮች የተነሳ፣ የነገረ-መለኮቱ ምሁራን ስለ አፃፃፋቸው ታሪክ በርካታ ጽንሰ ሃሳቦችን ነድፈዋል፡፡ እነዚህ ጽንሰ ሃሳቦች ውስብስብ ከመሆናቸው የተነሳ ልናጠናቸው ስንጀምር ግራ ያጋቡናል፡፡ ታዋቂ የሆኑትን ጽንሰ ሃሳቦች በዚህ መንገድ ጠቅለል ልናደርጋቸው እንችላለን፡ አብዛኞቹ ተርጓሚዎች እንደሚስማሙት ማርቆስ በመጀመሪያ ተጽፏል እናም ማቴዎስና ሉቃስ ከሌሎችም ምንጮች መጠቀማቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከእርሱ ብዙ መረጃዎችን አግኝተዋል፡፡ አንዳንዶች ግን ማቴዎስ አስቀድሞ ተጽፏል፣ ማርቆስም ከእርሱ ብዙ ወስዷል፣ ሉቃስ ደግሞ ከማቴዎስም ከማርቆስም ወስዷል ይላሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ማቴዎስና ሉቃስ እኛ ልናገኛቸው የማንችላቸውን ምንጮች ተጠቅመዋል እናም ማርቆስ ከሁለቱም ወስዷል ብለው ያምናሉ፡፡ እንዳያችሁት፣ የእነዚህን ጽንሰ ሃሳቦች አጠቃላይ ባሕርይ ስናነፃፅር እንኳር ግር የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በንፅፅር፣ የዮሐንስ አፃፃፍ ቀለል ያለ ነው፡፡ አብዛኞቹ ሊቃውንት እንደሚስማሙት እርሱ የጻፈው በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ማብቂያ ላይ በመሆኑ ቢያንስ ከተመሳሳዮቹ ወንጌላት አንዱን እንዲያውም ሁሉንም አግኝቷል በሚለው ይስማማሉ፡፡ ስለዚህም በተመሳሳዮቹ ወንጌላት እንደተነሱ ያወቃቸውን ነገሮች ከመድገም ይልቅ፣ ለሚያገለግለው ማኅበረሰብ ይጠቅማሉ የሚላቸውን አግባብነት ያላቸውን ተጨማሪ መረጃዎች ማስፈርን መርጧል፡፡

እነዚህን የአፃፃፍ ጽንሰ ሃሳቦች በልቡናችን ይዘን፣ እነርሱን አጥበቀን ልንይዝ ስለሚገባበት እርግጠኝነት እንነጋገራለን፡፡

## እርግጠኝነት

በመጀመሪያ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፍት በተደጋጋሚ ቃል በቃል ሲተላለፉ የኖሩትንና የተፃፉትን ትውፊቶች መጠቀማቸውን እውቅና ልንሰጥ ይገባል፡፡ ይህ ማለት ግን የመንፈስ ቅዱስ አብርተ መለኮት መሆናቸው ወይም ሥልጣናቸው ለድርድር ይቀርባል ማለት አይደለም፡፡ ስለዚህ የወንጌላት ጸሐፊዎች ቀዳሚ ምንጭ ተጠቅመዋል  በሚለው መርህ ማመን ምንም ስህተት የለበትም፡፡ ሉቃስ በምዕራፍ ፩፥፩-3 እንደፃፈው ማለት ነው፡፡

> የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ፥ ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፥ በኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ፥ እኔ ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ። (ሉቃስ ፩፥፩-3)

ሁሉም የወንጌላት ፀሐፊዎች ምንም እንኳን ሉቃስ እንዳደረገው ባይጠቅሱትም፣ ተመሳሳይ ምንጮችን ተጠቅመዋል፡፡ ብዙዎቹ ተርጓሚዎች የሚስማሙበትን ማርቆስ መጀመሪያ ተፅፏል የሚለውን እንውሰድና፣ ቀድመው የተፃፉ ወንጌላትን አላየም እንበል፣ ሆኖም ቢያንስ የቅርብ

ጓደኛው ከሆነው ከጴጥሮስ በቃል የሰማውን መጠቀሙ ግን እርግጥ ነው፡፡ ሉቃስና ማቴዎስ ግን የማርቆስን ወንጌል እንደ ሞዴል ተጠቅመውበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ ማቴዎስና ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ሕይወትና ትምህርቶች የራሳቸው የሆነ መረጃ አላቸው፡፡ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ደግሞ፣ አራቱም ፀሐፊዎች በማይሻር መንገድ በመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ የዘላለም ሃሳብ ውስጥ ነበሩ፡፡

ስናጠቃልለውም፣ በወንጌላት መካከል ስላለው ግንኙነት የተነደፉትን ፅንሰ ሃሳቦች እናደንቃለን፡፡ ሆኖም ግን ውስብስብነታቸውን ልቅም አድርገን ካልተረዳን ብለን ልንጨነቅ ወይም በአንዳቸው ላይ ሙጭጭ ልንል ጨርሶ አይገባንም፡፡ እነዚህ ጽንሰ ሃሳቦች የወንጌላት ፀሐፊዎች ከተለያዩ ምንጮች የመጠቀም ችሎታ እነደነበራቸው እና ስለ ኢየሱስ ሕይወትና አስተምህሮዎች ተዓማኒነት ያለው መረጃ እንዳዋቀሩልን በእርግጠኝነት እንድንረዳ ያደርጉናል፡፡ ዘገባዎቻቸው የተላለፉ ከመሰለንም የቱም ይቅደም የቱ፣ የወንጌላውያኑን የተለያየ አተያይ እውቅና የምንሰጥበትን እድል ይሰጡናል፡፡  በአንዱ ወንጌል ላይ ብቻ የሰፈረ ሃሳብ ስናነብብም፣ በዚያ ፀሐፊ ዓላማ ላይ ተመሥርተን ልናጠናው ይገባናል፡፡

የአራቱን ወንጌላት አፃፃፍ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ እውነተኝነታቸውን እንመለከታለን፡፡

# እውነተኝነት

በቤተክርስቲያን ቀደምት ዓመታት ውስጥ፣ በሐዋርያት ዘመን ከነበሩት መፃሕፍት መካከል የትኞቹ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይካተቱ በሚለው ነገር አለመስማማቶች ነበሩ፡፡ አንዳንድ የቀደምት ቤተክርስቲያን መሪዎች አሁን እኛ በአዲስ ኪዳን የምንጠቀምባቸውን መጻሕፍት ለሁሉም እውቅና አይሰጡም ነበር፡፡ ሌሎቹ ደግሞ እንዲያውም ከሃያ ሰባቱ ሌላ ልናካትታቸው የሚገቡ አሉ ይላሉ፡፡

እነዚህ ሙግቶች ግን አራቱን ወንጌላት ማለትም ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስን አያካትቱም፡፡ የተቀሩት ግን በታመኑ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ እንኳን ሙሉ በሙሉ እንደ እውነተኛና ባለሥልጣን ቃል በሁሉም ዘንድ ተቀባይነትን አያገኙም ነበር፡፡

ለምሳሌ፣ የሦስተኛው ክፍለ ዘመን አባት የሆነውና ከ185 እስከ 232 ዓ.ም. የኖረው ኦሪገን፣  እኛ በአዲስ ኪዳን ካካተትናቸው መካከል አራቱ ብቻ እውነተኛ ናቸው የሚለውን ሙግት ያነሳ ነበር፡፡

ኦሪገን የቤተክርስቲያን ታሪክ ፀሐፊ በነበረውና ከ263 እስከ 340 ዓ.ም. በኖረው በኢዮሲበስ ተጠቅሷል፡፡ እስኪ Ecclesiastical History, በተሰኘው ስድስተኛ መጽሐፉ ምዕራፍ 25 ላይ ኢዮሲበስ ኦሪገንን ጠቅሶ የጻፈውን እናድምጥ፡

> **ከሰማይ በታች በምትገኘው የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን የማያከራክሩት .... አራቱ ወንጌላት ብቻ ናቸው፡፡**

በተጨማሪም፣ አንድ ምዕተ ዓመት ቀደም ብሎ ከ130 እስከ 202 ዓ.ም. የኖረው የቤተክርስቲያን አባት ኢራኒየስ Against Heresies በተሰኘው ሦስተኛው መፅሐፉ፣ ምዕራፍ 7 ክፍል 8 ላይ ስለ አራቱ ወንጌላት ሲናገር እንዲህ ፅፏል፡

**ወንጌላት አሁን ካሉበት ቁጥር እንዲቀንሱም ሆነ እንዲጨመርባቸው ማሰብ አይቻልም፡፡ ለሰው ልጆች የተገለጠው፣ እርሱም ኢየሱስ፣ አራት ገፅታ ያላቸውን፣ ግን በአንድ መንፈስ በአንድነት የተሳሰሩትን ወንጌላት ሰጥቶናል፡፡**

በቤተክርስቲያን አምልኮ ውስጥ እነዚህ አራቱ ያከራከሩበት አሊያም ከአራቱ ሌላ ወንጌል አገልግሎት ላይ የዋለበት ወቅት ስለመኖሩ እንደማያውቅ ኢራኒየስ ተናግሯል፡፡

## የታመኑ ፀሐፊዎች

የመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን በአራቱ ወንጌላት ላይ የማይናጋ መተማመን እንዲኖራት ያደረጉ ቢያንስ ሦስት ምክንያቶች አሉ፡፡ በመጀመሪያ፣ ቤተክርስቲያን አራቱን ወንጌላት እውነተኛ አድርጋ የተቀበለችው በስማቸው ከተጠቀሱት የታመኑ ፀሐፊዎች አንፃር ነው፡፡

ወንጌላት በመጀመሪያ ጊዜ ስም ያልነበራቸው ነበሩ የሚል ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሃሳብ አለ፡፡ ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲታተሙ፣ የተቀበሏቸው ሰዎች ፀሐፊዎቹን የሚያውቁ ሰዎች ነበሩ ወይንም የፀሐፊዎቹን ማንነት ከሚያስታውቁ ሾኒ ደብዳቤዎች ጋር ተሰራጭተዋል፡፡ እናም ቀደም ካሉት ጊዜያት አንስቶ፣ ክርስቲያናዊ ጽሑፎች ወንጌላትን ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ከሚሉ ስሞች ጋር ያያይዟቸው ነበር፡፡ አራቱ ሰዎች በአዲስ ኪዳን መልካም ስም ያላቸው የቤተክርስቲያን መሪዎች በመሆናቸው ይታወቃሉ፡፡

## ሐዋርያዊ ይሁንታ

ሁለተኛ፣ የቀደሙት ክርስቲያኖች ወንጌላት በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ካኖን ውስጥ ባላቸው ስፍራ ይተማመኑ የነበረው እነዚህ መጻሕፍት የሐዋርያትን ይሁንታ ያገኙ በመሆናቸው ነው፡፡

ማቴዎስና ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ንግሮችና ሥራዎች የዐይን ምስክሮች የነበሩ ሐዋርያት ናቸው፡፡ ማርቆስ ደግሞ ስለ እርሱ በ1ኛ ጴጥሮስ 5፥13 ላይ "**ልጄ**" በማለት በፍቅር ቋንቋ ከጠቀሰው ከጴጥሮስ አብዛኛዎቹን መረጃዎች ተቀብሏል ተምሯልም፡፡ እንደተመለከትነውም፣ ሉቃስ ደግሞ መረጃዎቹን ከዐይን ምስክሮች እንዳገኘ በሉቃስ 1፥1-4 ላይ አስፍሮታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ ኢዮሲቢስ Ecclesiastical History, በተሰኘው ሥራው ሐዋርያው ዮሐንስ የራሱን ከመጻፉ አስቀድሞ ሦስቱን ወንጌላት አረጋግጧል በማለት ዘግቧል፡፡ ኢዮሲቢስ በ3ኛው መጽሐፉ፣ ምዕራፍ 24 ላይ ስለ ሐዋርያው ዮሐንስ የጻፈውን አድምጡ፡

**ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ ተብለው የተጠቀሱት ወንጌላት በእርሱና በሌሎችም እጆች ውስጥ ገብተው ነበር፣ ስለዚህም የሚናገሩትን ተቀብሏል እና ስለ እውነተኝነታቸው ምስክርነትን ሰጥቷል፡፡**

## የቤተክርስቲያን ምስክርነት

ሦስተኛ፣ አራቱም ወንጌላት በቀደምት ቤተክርስቲያን ምስክሮች የተደገፉ ነበሩ፡፡ አራቱም መጻሕፍት ለኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት የዐይን ምስክሮች ለነበሩ ሰዎች ይሁንታም ሆነ ተቃውሞ ለመቀበል በቂ ዕድሜ ነበራቸው፡፡ የዐይን ምስክሮቹ ግን በቀደሙት ዓመታት ወንጌላትን በቤተክርስቲያን ውስጥ በመቀበል ይሁንታን ሰጥተዋቸዋል፡፡

*በቃሉ ውስጥ ለተጠቀሰው የራሱ ድምፅ እግዚአብሔር ይመሰክራል፡፡ እኛን ይረዳን ዘንድ ግን፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተጠቀሱትን ታሪካዊ ክስተቶች እንመለከታለን እናም ስለ ታሪክ ከሌሎች ምንጮች ጋር ከምናገኘው ነገር ጋር ይጣጣማሉ፡፡ ጠቅለል ባለው ሁኔታ ስንመለከተው፣ ወንጌላቱ ከተጻፉበትና በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በፓለስታይን ከነበረው ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ መልክዓምድራዊና ሌሎችም በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሱ ነገሮች ጋር የሚስማማ ታሪካዊ እውነታን እናገኛለን፡፡ ሆኖም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ለየት ያሉ ታሪካዊ ሁነቶችን እና የሚገልጡዋቸውን ነገሮች ስንመለከት ግን፣ መጥተንበታል በማለት ከሚናገሩበት ዘመን በእውን የወጡ መሆኑን እንድንረዳ አሳማኝ መሠረት ይሰጡናል፣ ደግሞም በመንፈስ ምስክርነት የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆናቸው እርግጠኞች እንሆናለን፡፡ ስለዚህም በቀደመችው ቤተክርስቲያን በመጀመሪያውና በሁለተኛው ምዕተ ዓመታት፣ ወንጌላት እንደምናውቀውም አራቱ ወንጌላት ከሐዋርያት የተገኙ ወይም ሐዋርያዊ ምንጮች ያሏቸው፣ ኢየሱስ ስላደረገው፣ ስለማንነቱና ስላስተማራቸው ነገሮች የታመነና እውነተኛ መረጃ የሚሰጡ መፃህፍት ሆነው ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡ [ቄስ ሚካኤል ግሎዶ]*

*ወንጌላት፣ ተዓማኒነት ያላቸው፣ እስትንፋሰ መለኮት፣ ቀጥተኛ የሆኑ ጭብጦችን ያዘሉ መሆናቸውን የምናምንባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉን፡፡ ከሁሉ ይልቅ ልናገር የምፈልገው፡ የዐይን ምስክሮቹ ምስክርነታቸውን በመኖር አፅንተውታል የሚለውን ነው፡፡ ከእነርሱ አንዳንዶቹ ተገርፈዋል፣ ተደብድበዋል፣ ወደ ወህኒ ተጥለዋል፣ ተሰቅለዋል፣ ከእነርሱ መካከል አንዱም እንዲህ ብሏል "በነገራችን ላይ፣ ታውቃላችሁ በእውነት ታሪክ ነው" ለተናገሩት ነገር ሞተውለታል፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀው ሰዎች ለመሞት የሚፈቅዱለት ነገር አለ … ሰዎች ስለ ውሸት ደጋግመው ሲሞቱ ይስተዋላሉ፡፡ ስለ ውሸት ከሞቱት ሰዎች አብዛኞዎቹ ግን የሞቱለት ነገር ውሸት መሆኑን አያውቁም፡፡ የሚሞቱለት ነገር ውሸት መሆኑን እያወቁ የሚሞቱ ሰዎች ቁጥራቸው አናሳ ሲሆን እነርሱም ቢሆን በሕይወት ዘመናቸው ኃይልን ወይንም ብልጥግናን ወይንም ዝናን ያስገኝልናል ብለው ሲያምኑ ነው፡፡ እነርሱ ግን ከነዚያ አንዳቸውንም አላገኙም፡፡ በዚህ ዓለም እንደ ምናምን ተቆጥረዋል፣ ያለማቋረጥ በሩጫው ላይ ነበሩ፣ ደህይተዋል፣ ተሰውተዋል፣ ተደብድበዋል ከዚያም ሞተዋል፡፡ አንዳቸውም ምስክርነታቸውን አልካዱም፡፡ ስለዚህ የተከናወነ ለመሆኑ እርግጠኞች እንሆናለን፡፡ [ዶ/ር ዳን ዶሪያኒ]*

# አንድነት

የወንጌላትን ስነ-ጽሁፋዊ ባህርይ መርምረናል ደግሞም በቤተክርስቲያን የነበራቸውን ስፍራ ተመልከተናል፣ አሁን ደግሞ በአዲስ ኪዳን ወንጌላት መካከል ያለውን አንድነት ለመመልከት ተዘጋጅተናል፡፡

አስቀድመንም በወንጌላት መካከል ያለውን አንድነት ሁሉም መጻሕፍት ስለ አንድ የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ የሚናገሩ መሆኑን በመነጋገር እንጀምራለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ የአግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ምድር በሚያመጣው በኢየሱስ ላይ አፅንዖት እንሰጣለን፡፡ እንግዲህ አስቀድመን በአራቱም የአዲስ ኪዳን ወንጌላት ገዢ በሆነው ታሪክ እንጀምር፡፡

## ተመሳሳይ ታሪክ

ጠቅለል ባለው መረዳት፣ በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስና በዮሐንስ ወንጌላት የተነገረው ታሪክ ወንጌል ነው ማለት እንችላለን፡፡ በእርግጥም፣ መጻሕፍቱ በቀጥታ "**ወንጌላት**" ተብለው የተጠቀሱት ለዚህ ነው፡፡ እንግዲያው መጽሐፍ ቅዱስ ስ ኢየሱስ ወንጌል ሲናገር የሚናገረው ስለ ኢየሱስ ስለሚነገረው የምሥራች ነው፡፡ ግን ይህ የምሥራች በእርግጥ ምንድን ነው? ኢየሱስስ ማን ነው? ወንጌላትስ ስለ እርሱ የሚነግሩን ታሪክ ምንድን ነው?

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ፣ "ወንጌል" የሚለው ቃል በጥንታዊው ዓለም ውስጥ ለአንዳንድ ውስን ዓይነት ዜናዎች አገልግሎት ላይ ይውል እንደነበረ ልንረዳ ይገባናል፡፡ በተለይ ደግሞ፣ ተዋጊ ነገሥታት አዲስ ግዛቶችን ድል በሚያደርጉበት ወቅት፣ "መልካም የምሥራች" በሚል ቃል ንጉሣዊ የድል አዋጃቸውን ያሳውጁ ነበር፡፡ በዚህ "ወንጌል፣" "የምሥራች" በሚለው ቃል አጠቃቀም ውስጥ የንጉሡ ድል ነሺነትና ንግሥና ለህዝቡ የሚያስገኛቸው በረከቶችም ይታወጁበታል፡፡ እንዲያውም፣ ይህ ቃል በብሉይ ኪዳንም አገልግሎት ላይ ይውል የነበረውም እንዲሁ ነበር፡፡

ለምሳሌ፣ በኢሳያስ ምዕራፍ 52፥7

> የምስራች የሚናገር፥ ሰላምንም የሚያወራ፥ የመልካምንም ወሬ የምስራች የሚናገር፥ መድኃኒትንም የሚያወራ፥ ጽዮንንም። አምላክሽ ነግሦአል የሚል ሰው እግሩ በተራሮች ላይ እጅግ ያማረ ነው። (ኢሳያስ 52፥7)

በዚህ ምንባብ፣ ኢሳያስ ያየው ራዕይ የእስራኤል የምርኮ ዘመን ያለፈ መሆኑን የሚያውጀው የምሥራች አብሳሪ እግሮች በኢየሩሳሌም ተራሮች ላይ የሚራመድበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ መልዕክተኞቹ እግዚአብሔር በመንገሡ የሚመጣውን ሰላምና ድነት ያውጁ ነበር፡፡

በኢሳያስ ትንቢት አውድ መሠረት፣ የእግዚአብሔር ንግሥና፣ መንግሥቱንም በምድር ላይ የመመሥረቱ ነገር የእስራኤል እና የይሁዳ ሕዝቦች ሊሰሙ የሚገባው መልዕክት ነው፡፡ በእግዚአብሔር ንግሥና ስር፣ ከጠላቶቻቸው እጅ አርፈው በምድር ላይ እግዚአብሔር በሚመሠርተው መንግሥቱ ስር እንደሚኖሩ የሚውጅ ዜና ነው፡፡

በኢሳያስ ዘመን ግን፣ እግዚአብሔር ይህን ነገር አልፈፀመውም፡፡ የኢሳያስ ትንቢት እግዚአብሔር በምድር ላይ መንግሥቱን ለመመሥረት በኃይል የሚመጣበትን የወደፊት ጊዜ የሚያመለክት ነበር፡፡ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ያወጁት የምሥራች የሚነግረን ይህ መንግሥት በኢየሱስ የመጣ መሆኑን ነው፡፡ ሁሉም የወንጌላት ፀሐፊዎች የሚነግሩን ተመሳሳይ ታሪክ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያመጣ እና የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን የፈፀመ መሆኑን ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ምድር የመጣበት የመጨረሻው ንጉሥ ኢየሱስ የመሆኑን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እጅግ ያማሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ይህ የሚመጣውን መንግሥት የሚውጀው ታሪክ ወንጌላትን ሁሉ አንድ የሚያደርገው ገዢ ሃሳብ ነው፡፡

በዚህ እውነታ ብርሃን መሠረት፣ የአዲስ ኪዳን ወንጌላት "**ወንጌል**" እና "**ወንጌልን ማዳረስ**" የሚለውን ቃል የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመግለጥ የተጠቀሙት በጣም ባነሰ መጠን መሆኑ ሊያስደንቀን አይገባም፡፡ በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስና በዮሐንስ ውስጥ "**ወንጌል**" የሚለው ቃል በተለያየ ቅርፅ የሚገኘው በ23 ጥቅሶች ውስጥ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ተቃራኒ ግን፣ "**ንጉሥ**"፣ "**የእግዚአብሔር መንግሥት**" የሚለው ሐረግ በተለይም ማቴዎስ የተጠቀመበት ልዩ ሐረግ "**መንግሥተ ሰማያት**" የሚለው ግን 150 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል፡፡

ሁሉም ወንጌላት የእግዚአብሔር መንግሥት ስለተሰኘው ተመሳሳይ ታሪክ የሚናገሩ መሆኑን ከተረዳን፣ አሁን ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት በሚያመጣው ንጉሥ በኢየሱስ ላይ የሰጡትን አፅንዖት እንመልከት፡፡

# ኢየሱስ

ስለ ኢየሱስና ስለ መንግሥት የምንነጋገርበትን ሃሳብ በሦስት የተከፈለ ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ መንግሥትን የሚመጣ ስለመሆኑ ወንጌላት የሚቀርቡልንን ጥቂት ማረጋገጫዎች እንመከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ ስለ ኢየሱስና ስለ መንግሥት መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቀምበትን ቃል ትርጉም እናብራራለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ኢየሱስ መንግሥትን የሚመጣው በተለያዩ እርከኖች መሆኑን እናያለን፡፡ እስኪ ኢየሱስ መንግሥትን እንደሚመጣ የሚያመለክቱ ማረጋገጫዎችን በመመልከት እንጀምር፡፡

## ማረጋገጫዎች

የእግዚአብሔር መንግሥት በኢሱስ ውስጥ እንደምትመጣ ወንጌላት የሚያረጋግጡባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ እኛ ግን በዚህ ትምህርት በሦስቱ ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት በመጀመሪያ የምንጠቅሰው ማረጋገጫ ኢየሱስ በአጋንንቶች ላይ ያለው ኃያልነት ነው፡፡ በማቴዎስ 12፥28 ኢየሱስ የተናገረውን አድምጡ፡

> እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች። (ማቴ 12፥28)

በዚህ ምንባብ፣ ኢየሱስ አጋንንትን አስወጥቷል፡፡ አጋንንትን የማስወጣት ብቃቱም የእግዚአብሔርን መንግሥት የማምጣቱ ማረጋገጫ ነው፡፡

ወንጌላት የእግዚአብሔር መንግሥት ስለ መምጣቷ የሚገልጡበት መንገድ ኢየሱስ ህመምተኞችን ለመፈወስና ሙታንን ለማስነሣት ያለውን ኃይል ነው፡፡

ወንጌላት አዘውትረው የሚያመለክቱትና ኢየሱስ በሽተኞችን ለመፈወስ ያለው ኃይልና ለደቀመዛሙርቱም የሰጣቸው ተመሳሳይ ኃይል የእግዚአብሔርን መንግሥት ያመጣ የመሆኑ ማረጋገጫ ነው፡፡ ይህንንም መሪ ሃሳብ በማቴዎስ 4፥23-24፣ 8፥5-13 እና 10፥7-8 ውስጥ እናየዋለን፡፡ በተጨማሪም በሉቃስ 9፥1-11 እና 10፥9 እና በሌሎችም በርካታ ስፍራዎች እናየዋለን፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣቷን ኢየሱስ ኃጢአትን በማስተሰረይ ሥልጣኑም ውስጥ እንመለከተዋለን፡፡

ኢሳያስ በትንቢቱ ምዕራፍ 33፥22-24 ውስጥ ስለሚመጣው መሲህ የተናገረውን አድምጡ፡

> እግዚአብሔር ፈራጃችን ነው፥ እግዚአብሔር ሕግን ሰጪያችን ነው፥
> እግዚአብሔር ንጉሣችን ነው እርሱ ያድነናል።
> ገመዶችህ ላልተዋል፥ ደቀላቸውንም አላጸኑም፥ ሸራውንም መዘርጋት
> አልቻሉም። በዚያም ጊዜ የብዙ ምርኮ ብዝበዛ ተከፈለ አንካሶች እንኳ
> ብዝበዛውን በዘበዙ።
> በዚያም የሚቀመጥ። ታምሜአለሁ አይልም፥ በእርስዋም ለሚቀመጡ ሰዎች
> በደላቸው ይቅር ይባልላቸዋል። (ኢሳ 33፥22-24)

ኢሳያስ ያመለከተው መፈወስና ይቅር ማለት የእግዚአብሔር ንጉሣዊ ሥልጣኑ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህም በስተመጨረሻው ፈውስና ይቅርታ በመሲሁ በኩል እንደሚመጣ ያም የሚሆነው መሲሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ሲመሠርት መሆኑን ተንብዮአል፡፡

ኢየሱስም ያደረገው ይህንኑ ነው፡፡ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲገቡ ጠርቷቸዋል፡፡ በሞት ፈንታም ሕይወትን ሰጥቷል፡፡ ልእክቱም የድነት፣ ከኀጢአት ነፃ የመውጣት መልእክት ነው፡፡ በማርቆስ 2፥9-11 ኢየሱስ ያደረገውን ንግግር አድምጡ፡

> ሽባውን። ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ከማለት ወይስ። ተነሣ አልጋህንም
> ተሸከምና ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል?
> ነገር ግን ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ሊያስተሰርይ ሥልጣን እንዳለው
> እንድታውቁ፤
> ሽባውን። አንተን እልሃለሁ፥ ተነሣ፥ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ
> አለው። (ማር 2፥9-11)

ኢየሱስ እንደ ሰው ልጅ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማምጣቱንና በምድርም ኀጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣን እንዳለው ሲያውጅ ሲያውጅ ሁሉን አስገርሟል፡፡

በኢየሱስ በኩል የእግዚአብሔር አገዛዝ መጥቷል፡፡ የእግዚአብሔር ንግሥና፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር እዚህ ሆና ነበር፡፡ ያም ማለት ለእግዚአብሔር ሕዝብ በረከት ሆኖ ነበር፡፡ ማለትም ኢሳያስ ከዓመታት በፊት የተነበየው የእግዚአብሔር ሰላም፣ በመጨረሻው መጥቶ ነበር ማለት ነው፡፡

እነዚህን ማረጋገጫዎች በልቡናችን ይዘን፣ ወንጌላት ስለ ኢየሱስና ስለ መንግሥት ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸውን ቃላት እንመልከት፡፡

# ቃላት

ወንጌላት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የሚሰጡትን አፅንዖት ክርስቲያኖች በቀላሉ የማያበት አንዱ ምክንያት የወንጌላት ፀሐፊዎች ስለ እርሱ ሲናገሩ የተለያዩ ቃላትን የሚጠቀሙ በመሆናቸው ነው፡፡ "ንጉሥ" እና "መንግሥት" የሚሉ ቃላት በግልጽ ተጠቅመዋል፡፡ ነገር ግን ደግሞም "ንግሥና" "አገዛዝ" "ሥልጣን" "ዙፋን" "የዳዊት ልጅ" የመሳሰሉና ሌሎችንም ቃላት የእግዚአብሔርን አገዛዝና ሉዓላዊነት ለመጥቀስ ተጠቅመዋል፡፡

> ***የአዲስ ኪዳን ፀሐፍት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሲናገሩ የተለያዩ ቃላትን ተጠቅመዋል፣ ይህንንም ሲያደርጉ ግልፅና ቀጥተኛ የሆኑትን ብቻ ሳይሆን ተዛማጅ የሆኑ ሃሳቦችንም ተጠቅመዋል፡፡ ለምሳሌ፣ ክርስቶስ የሚለው ለኢየሱስ የተጠቀሙበት ማዕረግ፣ ፍቺው "መሲህ"፣ "የተቀባው"፣ ማለት ሲሆን፣ ያም በብሉይ ኪዳን ስለ ንጉሥ፣ ስለ ዳዊት ልጅ የሚናገር ቋንቋ ነው፡፡ ወይንም ደግሞ kurios ወይም Lord የሚለው ቃል እንደገናም ለኢየሱስ የተሰጠ ማዕረግ ሲሆን ይህም እርሱን እንደ ንጉሥ የሚገልፅ ነው፡፡ ቄሳርም ይህንን ማዕረግ ይጠቀም ነበር፡፡ እንግዲያው፣ የአዲስ ኪዳን ፀሐፍት በነበሩበት ዘመን አውድ መሠረት፣ "ጌታ" በሚለው ቃል ውስጥ የሚገለጠውን ሥልጣን ሰዎች በውል ይረዱት ነበር ማለት ነው፡፡ እርግጥ ነው፣ እጅግ ወሳኝ የሆነው ሐረግ "የእግዚአብሔር መንግሥት" ወይንም በማቴዎስ አገላለጥ "መንግሥተ ሰማያት" የሚለው ነው፡፡ ያም ሐረግ በሁለት መንገዶች ይገለፃል፡፡ ክርስቶስ በህዝቡ ላይ ያለውን አገዛዝ የሚያሳይ ሲሆን፣ ከዚያም በተጨማሪ ግን የእግዚአብሔርን ንግሥና፣ ማለትም እግዚአብሔር በህዝቡ ላይ ያለውን ሥልጣን የሚያመለክት ገላጭ ቃል ነው፡፡ ስለዚህ፣ ከዚህ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሃሳቦች ለምሳሌ መታዘዝ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ከሚለው ጋር ቀጥተኛ ተጠቃሽ ቃል አይደለም ሆኖም ከንጉሡ ሥልጣን ጋር ግን ጉድኝትና አንድምታ አለው፡፡ ያም ከኢየሱስ ጋር በተያያዘ እርሱን ከመታዘዛችን እንዲያውም ከማምለካችን ጋር ይገናኛል፡፡ [ዶ/ር ግሬግ ፔሪ]***

አንድ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፣ በማርቆስ ወንጌል 2፥1-12 የተጠቀሰው ኢየሱስ ሽባውን በፈወሰበት ታሪክ "ንጉሥ" ወይንም "መንግሥት" የሚሉትን ቃላት አልተጠቀሰም፡፡ ሆኖም ግን፣ ቁጥር 10፣ የጠቅላላ ታሪኩን የመንግሥት ፍቺ እንድናይ ግድ ይለናል ያም ኢየሱስ "የሰው ልጅ

**በምድር ኃጢአትን የማስተሰረይ ሥልጣን አለው”** ብሎ ሲናገር ተጠቅሷል፡፡ በኢየሱስ የመፈወስና ኃጢአትን የማስተሰረይ ሥልጣን ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ምድር መጥታለችና፡፡ በእርግጥም፣ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ኢየሱስ የሚያከናውናቸው በጎ ተግባራት በጠቅላላ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ቅምሻዎች የነበሩ ሲሆን፣ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችም የከበረውንና የተባረከውን የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያመለክቱ ነበሩ፡፡

> *ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የመምጣት ተስፋና ጥበቃ አንፃር በብሉይ ኪዳን በተለይም በኢሳያስ መጽሐፍ እንደተጠቀሰው፣ እግዚአብሔር ወደ ምድር መጥቶ የመንገሡና የመግዛቱና መንግሥቱን የመመሥረቱ ተስፋ የንዳሴ ዘመን ተስፋ ሲሆን፣ ይህም ሁሉ ደህና የሚሆንበት መንግሥት እንደሆነ ያሳየናል፡፡ በኢየሱስ የፈውስ አገልግሎትና በወንጌላት ተከናውነው ከምናያቸው ነገሮች አንዱም የፈውስ አገልግሎቱንና ሰዎችን የማደስ ሥራውን፣ የሞተውን ማስነሣቱን፣ የሰዎች የደም መፍሰስ ማቆሙን፣ የኀበጠውን ወገብ ማቅናቱን፣ የታወረውን ማብራቱን ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች የኢየሱስን ኃይልና ሥልጣን በዐቃቤነት የሚረጋግጡ ብቻ አይደሉም፣ አሊያም ደግሞ የእግዚአብሔር ኃይል መገለጫዎች ብቻም አይደሉም፣ በእርግጥም የእግዚአብሔር የንግሥና ተስፋ፣ የህዳሴው መንግሥት እንደሚመጣ፣ አሁንም በኢየሱስ እንደመጣ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ተብሎ የተጠቀሰው ቋንቋ ባይኖር እንኳን የእግዚአብሔር መንግሥት የሚያከናውናቸውን በርካታ ነገሮች ከምናይባቸው ነገሮች አንዱ ይህ ነው፡፡ [ዶ/ር ጆናታን ፔኒንግተን]*

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማምጣቱን የሚያረጋግጡልንን ማስረጃዎች ተመልክተናል፣ ደግሞም ወንጌላት ስለ ኢየሱስ መንግሥት ሲናገሩ የተጠቀሙባቸውን ቃላት ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ በአጭሩ ኢየሱስ መንግሥትን የሚመጣባቸውን ደረጃዎች እንመልከት፡፡

## ደረጃዎች

አሁን የምናየውና በኢየሱስ የመጣው  የእግዚአብሔር መንግሥት ልምምድ ሙሉ ምስሉ እንዳልሆነ ኢየሱስ አስተምሯል፡፡ ሌላኛው የመንግሥቱ ደረጃ ገና ይመጣል፡፡ ወደ ፊት በአንድ ወቅት ላይ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በሙሉ ማንነቱ ይገለጣል፡፡ ኢየሱስም ይህን የወደፊት ቀን በሉቃስ 21፥27-28 ላይ ገልጧል፡

> በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በኃይልና በብዙ ክብር በደመና ሲመጣ ያዩታል።
> ይህም ሊሆን ሲጀምር ቤዛችሁ ቀርቦአልና አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሡ።
> (ሉቃስ 21፥27-28)

በርካታ የብሉይ ኪዳን የነገረ-መለኮት ሊቃውንት፣ ብሉይ ኪዳንን የተረጎሙት መሲሁ ሲመጣ፣ የቀደመውን፣ የኀጢአትና የሞት ዘመን ወዲያ አስወግዶ፣ በአዲሱ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘመን እንደሚተካው ለማስተማር ነበር፡፡

ኢየሱስ ግን መንግሥቱን በተለያዩ ደረጃዎች እንደሚያመጣ አመልክቷል፡፡ በምድር አገልግሎቱ ዘመን መንግሥቱን በይፋ አውጇል፡፡ አሁን በመንግሥተ ሰማይ ባለው ንግሥናው መንግሥቱ ቀጥሏል፡፡ ዳግም ተመልሶ ሲመጣም ሙላቱ ይገለጣል፡፡

*በአቡቀለምሲሳዊው ይሁዲነት፣ ሁሉም እውነታዎች፣ በሁለት ክፍለ ዘመናት ይከፈላሉ፡፡ የአሁኑ ክፉ ዘመንና የሚመጣው ዘመን ናቸው፡፡ የሚጠበቀውም እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን መንግሥቱ፣ በሚመጣው ዘመን፣ ሁሉን በድንገት፣ በቅፅበተ ዐይንና በፍፁምነት እንደሚያከናውን ነው፡፡ ወዲያም ከቅድመ እግዚአብሔር መንግሥት ዘመን ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር ዘመን እንሸጋገራለን፡፡ በአዲስ ኪዳን ማለትም እኛ የአዲስ ኪዳን የምፅዓት ዘመን ብለን የምንጠራው፣ በአቡቀለምሲሳዊው ይሁዲነት እንደተመለከተው፣ በሁለት ዘመናት ይከፈላል፤ የአሁን፣ ወይም "የመጣው" የመንግሥተ ሰማይ ዘመንና "የሚመጣው" የመንግሥተ ሰማይ ዘመን ናቸው፡፡ [ዶ/ር ዴቪድ ባወር]*

*ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ስንናገር፣ ደጋግመን የምንናገረው "እንደመጣች" ነው፣ ሆኖም ደግሞ ወደፊት የምትመጣውንም መንግሥት ተስፋ እናደርጋለን፡፡ እርግጥም ኢየሱስ፣"መንግስትህ በሰማያት እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን" ብለን እንድንጸልይ አስተምሮናል፡፡ እናም ንጉሡ ስለመጣ፣ በዚህ በምድር መንግሥቱን አውጇል መሥርቷልም የሚል አንድምታ አለው፡፡ ሆኖም መመለሱንም እንጠብቃለን፡፡ የክርስቶስ ዳግም ምፅአት ኢየሱስ በመጀመሪያ መምጣቱ ያከናወናቸው ተግባራት ሙሉ በረከት የሚገለጥበት እንድምታዎቹም በመጨረሻ የሚፈፀሙበት ቀን ይሆናል፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ አማኝ፣ ወንጌልን ይዞ በዚህ ምድር በሚወጣበት ጊዜ ሁሉ የንጉሡን ዳግመኛ መመለስ የማወጅ ሃላፊነት አለበት፡፡ እናም ሰዎች ሁሉ ለክርስቶስ ዳግም ምፅአት የተዘጋጁ እንዲሆኑ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡ እኛ እንዳማኞች በአሁኑ ዓለም ክርስቶስን ጌታችን የማድረግ እድል ብናገኝም፣ በእርሱ ንግሥና ስር ብንኖርም፣ በሙላት የሚገለጠውን ግን ገና እንጠብቃለን፣ ይህ ግን ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለፍጥረት ሁሉ ነው፡፡ [ዶ/ር ሲሞን ቫይበርት]*

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩ አይሁድ ከኢየሱስ ፊታቸውን ቢመልሱ አያስደንቅም፣ ምክንያቱም እርሱ የገለጠው መንግሥት እነርሱ የሚጠብቁትንና የሚፈልጉትን አይመስልምና ነው፡፡ እነርሱ የሚጠብቁት ንጉሥና መንግሥት የሮሜን መንግሥት የሚገለብጥና አይሁድንም ከሮም ጭቆና የሚያላቅቅ ነበር፡፡ ኢየሱስ ያንን ዓይነት ንጉሥ የመሆን ፍላጎት የሌለውነ መሆኑን ሲገልፅ፣ ብዙዎች ጀርባቸውን ሰጥተውት ሄዱ፡፡ ልክ በሉቃስ 17፥20-25 እና በዮሐንስ 6፥60-69 እንደምንመከተው ማለት ነው፡፡

በመሠረቱም፣ ይህ አለመቀበል በፍፃሜው ኢየሱስን ወደ መስቀል ሞት ወስዶታል፡፡ ከኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት የወንጌል አያዎዎች ታላቁ ወቅቱ የንግስናው ጠላትነት ጣሪያ የተገለጠበት ደግሞም የንግሥናውና የመንግሥቱ ድል የተረጋገጠበት መሆኑ ነው፡፡ ትንሣኤውና ዕርገቱም በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በንግሥና መንበሩ ለመቀመጥ የተጓዘበት መንገድ ነው፡፡ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1፥ 3 እንደዘገበው፣ በትንሣኤውና በእርገቱ መካከል ባሉት አርባ ቀናት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ደቀመዛሙትን ያስተማረው ለዚህ ነው፡፡

በማቴዎስ 28፥18፣ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ አስቀድሞ እንዲህ አስቀምጦታል፡፡

**ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል (ማቴ 18፥28)**

የእግዚአብሔር መንግሥት በወንጌላት ውስጥ ስለ ኢየሱስ ሕይወት የተመዘገቡት ክስተቶች የሚጠቃለሉበት የምሥራቹ ወንጌል መሪ ሃሳብ ነው፡፡ ወንጌሉም የሚያውጀው የምሥራች እግዚአብሔር ተስፋውን የፈፀመ፤ መንግሥቱም በኢየሱስ በኩል የመጣች መሆኑን ነው፡፡ የኢየሱስ ድል ነሺ ሕይወትም አንድ ቀን ተመልሶ መንግሥቱን ፍፁም እንደሚያደርግ፣ የበረከቱንም ሙላት ወደ እኛ እንደሚያመጣ ያረጋግጥልናል፡፡

# ልዩ ልዩ አይነት

በዚህ ትምህርታችን፣ ወንጌላትን ከስነ-ፅሁፋዊ ባህርያቸው፣ በቤተክርስቲያን ካላቸው ስፍራ አንፃር የዳሰስን ሲሆን አንድነታቸውን ተመልክተናል፡፡ በዚህም ነጥብ ስር፣ አንዳቸውን ከሌላቸው በሚለዩዋቸው ልዩ ልዩ ዐይነቶች ላይ እንነጋገራለን፡፡

እንደተመለከትነው፣ አራቱም ወንጌላት የእግዚአብሔርን መንግሥት መምጣት ተመሳሳይ ታሪክ ቢዘግቡም፣ ዘገባውን ያቀረቡት ሁሉም በየራሳቸው  መንገድ ነው፡፡ ይህንንም ልዩ ልዩ አይነት በሁለት ዋና መንገዶች እንመረምረዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ በወንጌላት የተፃፈውን ለማጣጣም ያለውን ግልፅ ችግር እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ የእያንዳንዱን ወንጌል ለየት ያለ ትኩረት እንመለከታለን፡፡ አስቀድመን ከግልፅ ችግሮቹ  እንጀምር፡፡

## ግልፅ ችግሮች

ወንጌላትን ስናነብብ፣ እንዳቸው ከሌላቸው ጋር ያላቸውን አስገራሚ አንድነት እንመለከታለን፡፡ ሆኖም፣ በብዙ ቦታዎች ወንጌላት ለየት ያሉ ነገሮችን እንደመዘገቡም እንመለከታለን፡፡ እርግጥ ነው እነዚህ ልዩነቶች እጅግ አነስተኛ ስለሆኑ በየትኛውም መስፈርት ተቃርኖ ተብሎ ሊጠራ በሚችል ደረጃ ጠንካሮች አይደሉም፡፡ እርግጥ ነው፣ ጥቂቶቹ አንዳንድ አንባቢዎችን ግር ያሰኛሉ፡፡ እጅግ ወሳኝ የሆኑትን ጥቂት የልዩነት ዓይነቶችን መመልከት የሚያስፈልገን ለዚህ ነው፡፡

## ቅደም ተከተል

በቀላሉ ከሚታዩ ልዩነቶች መካከል ዋነኛው ከቅደም ተከተል ጋር፣ ማለትም በተለያዩ ወንጌላት ሁነቶች የተመዘገቡበት ቅደም ተከተል  ነው፡፡

እንደ የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ፣ እያንዳንዱ ወንጌል የሚከተለው ተመሳሳይ የጊዜ መስመር ነው፡፡ ሁሉም በኢየሱስ ልደት ይጀምራሉ፣ ከዚያም ወደ ሞቱ ይሻገራሉ በመጨረሻም ወደ ትንሣኤው ያመራሉ፡፡ በኢየሱስ ሕይወት ተከናወኑ ሁነቶችን ግን በተለያየ ቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ወንጌላት ሁነቶችን የሚያቀናጁት በሚሰጡት ቅድሚያ ሲሆን ይህም ለመጀመሪያው ቀቀክፍለ ዘመን ተደራሲያን ተቀባይነት አለው የእኛን ዘመን ጥበቃ ግን ላያሟላ ይችላል፡፡ ወንጌላት ቅደም ተከተልን ተቀዳሚ ከማድረግ ይልቅ፣ ልዩ ልዩ ሁነቶችን በመሪ ሃሳብና

በመልክዓምድር ላይ ቅደም ተከተላቸውን አሳርፈዋል። ለምሳሌ፣ ማርቆስ በምዕራፍ 6፥1-6 የኢየሱስን ታሪክ የሚነግረን በገዛ ከተማው ተቀባይነት ያጣ ከመሆኑ አንስቶ ነው። ሉቃስ ግን ይህን የሚነግረን በታሪኩ ገፋ ብሎ በምዕራፍ 4፥14-30 ባለው ውስጥ ይሆናል፣ ስለዚህ ታሪኩ በኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት ውስጥ የመጀመሪያው ታሪክ ነው ማለት ነው። ሉቃስ ከማርቆስ ይልቅ ታሪኩ ወሳኝ እንደሆነ ያሳያል። እንዲያውም የመገፋትን መሪ ሃሳብ በሚያጎላ መልኩ ታሪኩን ረዘም አድርጎ ያቀርበዋል።

የወንጌላቱ ጸሀፊዎች ኢየሱስ ወደ አገልግሎት የገባበትን ቅደም ተከተል ዋነኛ ከማድረግ ይልቅ በትምህርቶቹና በተግባራቱ የመንግሥቱን መምጣት በግልፅ ማስቀመጥን መርጠዋል።

## አለማካተት

ሁለተኛው ዓይነት ልዩነት ደግሞ በአንዱ ወይም ከዚያን በላይ ወንጌላት አንዳንድ ጉዳዮች አለመካተታቸው ነው። ለምሳሌ፣ የጌታን እራት ስርዓት ዮሐንስ በወንጌሉ ውስጥ አላካተተም። ይህ ዓይነቱ አለማካተት በብዙ መንገዶች ሊገለፅ ይችላል። በቀላሉ ከፀሐፊው የትኩረት አቅጣጫ አንፃር ሊሆን ይችላል። አሊያም የኋለኞቹ ፀሐፊዎች የፊተኞቹ የጻፏቸውን ደግመው መፃፍ አላስፈላጊ መሆኑን አይተው ሊሆን ይችላል። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን፣ የአንዳንድ ነገሮች አለመካተት በወንጌላት ጸሐፊዎች መካከል አለመስማማት ወይም ቅራኔ አለ ማለት አይደለም።

እስኪ እናንተ ከተለያዩ ሰዎች ጋር ስላደረጋችኋቸው ንግግሮች አስቡ። ንግግር የሚያደርጉ ሰዎች አንድ ሰው ቀድሞ የተናገረውን ነገር ሁሉ ደግሞ መናገር አስፈላጊ እንደሆነ ላይሰማቸው ይችላል። በምትኩ ግን፣ እያንዳንዱ ሰው በግሉ አተያይ ላይ አፅንዖት መስጠትን፣ አዲስ ዝርዝር ማቅረብን ምናልባትም ለየት ያለ አፅንዖት መስጠትን ሊመርጥ ይችላል።

ቅዱሳት መጻሕፍትም በየዘመናቱ ያደረጉት ይህንን ነው። ለምሳሌ፣ በ2ኛ ዜና 9፥29 ላይ፣ ዘጋቢው ሌሎች ፀሐፍት ቀደም ብለው የጻፉትን ዝርዝር አለማካተቱን ይጠቅሳል። ይህም ነገሮች በለየሎችም የ2ኛ ዜና መዋዕሎች ቢያንስ ለሦስት ጊዜ ተጠቅሷል። በ1ኛ እና በ2ኛ ነገሥት መጻሕፍትም በተደጋጋሚ እናያለን። ስለዚህ አንድ የወንጌል ጸሐፊ በሌሎች አስቀድመው የተፃፉ ወሳኝ ነገሮችን አለማካተቱ አስገራሚ ሊሆን አይገባም ማለት ነው።

## የተለያዩ ድርጊቶች

ግልፅ ከሆኑት አስቸጋሪ ነገሮች ሦስተኛው በኢየሱስ አገልግሎት ከተከናወኑት መካከል በተመሳሳይ ድርጊቶች መካከል የሚታየው የአመዘጋገብ ልዩነት ነው። ያም ማለት፣ አንዳንድ ጊዜ ወንጌላት ተመሳሳዩን ድርጊት በተለያየ መንገድ የሚያቀርቡት ይመስላሉ፣ ሆኖም የገለፁት ሁለት የሚመሳሰሉ ግን የተለያዩ ድርጊቶችን ነው።

ኢየሱስ ተዘዋዋሪ ሰባኪ እንደነበረ ማስታወሱ ጠቃሚ ነው። ያም ማለት ከቦታ ቦታ ይዘዋወር ነበር ማለት ነው። በተለያዩ ቦታዎችም በርካታ ተመሳሳይ ተዓምራትን አድርጓል፣ ዕውር ወይንም

አንካሶችንም ፈውሷል፡፡ በእርግጥም፣ ኢየሱስ ለበርካታ ተመሳሳይ ጥያቄዎችና ተግዳሮቶች ደግሞ ደጋግሞ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ ሰዎችም ለኢየሱስ በተለያዩ አጋጣሚዎች ተመሳሳይ ምላሾችንም ሰጥተዋል፡፡ እስኪ በሉቃስ 7፥36-50 እና በማርቆስ 14፥3-9 ኢየሱስ በዘይት የተቀባበትን ሁኔታ እንመልከት፡፡ በሉቃስ ኢየሱስ የነበረው በፈሪሳዊው ቤት ሲሆን፣ በማርቆስ ግን በለምፃሙ በስምዖን ቤት ነበር፡፡ እነዚህ የአንድ ተመሳሳይ ድርጊት የሚቃረኑ ዘገባዎች አይደሉም፡፡ በምትኩ ግን፣ የሁለት የተለያዩ ድርጊቶች ዘገባዎች ናቸው፡፡

## የተለያዩ ንግግሮች

አራተኛውና ግልፅ የሆነው አስቸጋሪ ነገር ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው የተለያዩ ንግግሮች የሚፈጥሩት ነው፡፡

ለዚህ ተመራጭ የሚሆነው ምሳሌ በማቴዎስ 5፥1-7፥29 የሚገኘው የኢየሱስ የተራራው ስብከት ሲሆን፣ ሉቃስ ደግሞ የዚህኑ ተመሳሳይ ትምህርት በሉቃስ 6፥17-49 ጠቅሶታል፡፡ በማቴዎስ 5፥1፣ ትምህርቱ የተሰጠው በተራራ ላይ እንደሆነ ይነግረናል፡፡ በሉቃስ 6፥17 ግን፣ ለጥ ባለ ስፍራ እንደተከናወነ ይነግረናል፡፡

ይህንን ችግር የምንጋፈጥባቸው ቢያንስ ሦስት መንገዶች አሉ፡፡ አንደኛ፣ ማቴዎስና ሉቃስ እየነገሩን ያሉት በአንድ ወቅትና ቦታ ስለቀረበ ስብከት ሊሆን ይችላል፡፡ የገሊላ ባህር ደቡብ ምዕራባዊ ክፍል ወጣ ገባ የሆነ ተራራማ አይደለም፣ ከባህሩ ተነስተው ዱታዩ ኮረብታዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ኮረብታማ ስፍራዎች ትናንሽና ለጥ ያሉ ስፍራዎችም አሏቸው፣ እንግዲያው ያው ተመሳሳዩ መልክዓ-ምድር በማቴዎስ እንደምናገኘው ተራራማ፣ በሉቃስ እንደምናገኘው ደግሞ ለጥ ያለ ስፍራ ሊሆን ይችላል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ምናልባትም በጥንት ዘመን ይደረግ የነበረው የተውጣጣ ስብከት ማለትም ኢየሱስ በተለያዩ ስፍራዎች የሰጣቸውን ትምህርቶች በአንድ አውጣጥቶ የማቅረብ ልምምድ ምሳሌ ሊሆን ይችል ይሆናል፡፡ ይህም በጥንት የታሪክ ፀሐፊዎች አገልግሎት ላይ ይውል የነበረ ቴክኒክ ሲሆን መቼም ቢሆን የግድፈትና የተዓማኒነት ጥያቄ ቀርቦበት አያውቅም፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ፣ ኢየሱስ ሁለት ተመሳሳይ መልእክቶችን በሁለት የተለያዩ ቀናት፣ በሁለት የተለያዩ መቼቶች፣ ማለትም አንዱን በተራራ ላይ ሌላውን ደግሞ ለጥ ባለ ስፍራ ላይ ሰብኮ ሊሆን ይችላል፡፡ በኢየሱስ አገልግሎት ዘይቤ ምክንያት ለእርሱ አዲስ የሆኑና ለማያውቁት ሰዎች ተመሳሳይ መልእክቶችን በድጋሚ ማቅረቡ አጥጋቢ ምክንያታዊነት ነው፡፡

በወንጌላት መካከል ያሉ ልዩነቶችን በተለያዩ መንገዶች መመልከታችን፣ የኢሱስ ሕይወትና አገልግሎት እውነተኛ መሆኑን የሚመሰክሩ ውብ ኅብረ-ቀለማት እንደሆኑ እንድናይ ያደርገናል፡፡ አዎን፣ በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ክፍተቶች መኖራቸው ትክክል ነው፡፡ ግን ለነዚህ የተለያዩ ልዩነቶች በቂ ማብራሪያዎችም አሉ፡፡ እናም ኢየሱስ በተለያዩ ወቅቶች ተመሳሳይ ነገሮችን ሲያስተምር ካገኘን፣ የአገልግሎቱንና የመልእክቱን ወጥነት የምንመከት ሲሆን፣ ትምህርቶቹንም በሕይወታችን ተግባራዊ የምናደርግበትን በርካታ መንገዶች እናገኛለን፡፡

በአራቱ ወንጌላት መካከል ያለውን ልዩ ልዩ ዓይነት በየምንባቦቹ ያሉትን ግልፅ አስቸጋሪ ነገሮች በመጠየቅ መመልከት ጀምረናል፡፡ ስለዚህ፣ አሁን ደግሞ፣ የአራቱን ወንጌላት ልዩ ልዩ ዓይነቶች ልዩ አፅንዖት የሰጧቸውን ነገሮች መመልከታችንን እንቀጥላለን፡፡

# ልዩ አፅንዖት

ወንጌላት የኢየሱስን ሕይወትና አገልግሎት በየራሳቸው አአተያይና ግድ በሚሏቸው ነገሮች ዙሪያ በዳሰሱ በተለያዩ ፀሐፍት በመጻፋቸው ምክንያት፣ በአራቱ ወንጌላት ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ አራቱም ወንጌላት በመንፈስ ቅዱስ መነዳት የተፃፉ መሆኑን በማወቅ፣ እያንዳንዳቸው አንዳችም እንከን እንደማይኖርባቸውና አንዱ ሌላውን እንደማይቃረን እርግጠኞች እንሆናለን፡፡ ይህ ማለት ግን ልዩነቶች የሉም ማለት አይደለም፡፡ መንፈስ ቅዱስ የሰብዓዊ ፀሐፍትን ስብዕናዎችን፣ መሻቶችን እና የአገልግሎት ሁኔታዎችን በመጠቀም ልዩነቶቹን ቅርፅ ሰጥቷቸዋል፡፡ ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እኛን መባረክ በሚፈልግበት መንገድ ለመባረክ ከፈለግን፣ ወንጌላቱን በምናነብበት ወቅት የየራሳቸው የሆኑትን አቀራረቦች ልብ ማለት ይገባናል፡፡

በሕይወት ገጠመኞቻችን፣ የተለያዩ ሰዎች አንድን እውነት በተለያየ መንገድ ሲገልፁ እናገኛቸዋለን፡፡ ትንንሽ ልጆች ሲጫወቱ የሚከታተል ሰው አንዱ ድርጊት የተለያዩ፣ ደግሞም የሚስማሙ አተረጓጎሞች ሊኖሩ እንደሚችሉ ያውቃል፡፡ እያንዳንዱ ልጅ ስለሚጫወተው ጨዋታ የራሱ አመለካከት አለው፡፡ በትክክል ምን እየሆነ እንዳለ ማወቅ የምንችለው እያንዳንዳቸውን በማግኘት ካደመጥናቸው ነው፡፡ ምናልባት አንዱ የአሻንጉሊቶቹ ኅብረቀለማትአስገርመውት ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላኛው ደግሞ ምናልባት የሚያሰሟቸው ድምፆች ደስ ሊያሰኘው ይችላል፡፡ ሌላው ደግሞ በዙሪያቸው ስለመሽከርከር እየተደነቀ ሊያወራን ይችላል፡፡ እነዚህ የተለያዩ አመለካከቶች እርስ በርስ የሚጣረሱ አይደሉም፡፡ ግን እያንዳንዱ ልጅ ከጫወታው መሃል ከሌሎቹ ይልቅ እርሱን ይበልጥ የሚስበውን ነገር ማግኘቱን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

በተመሳሳይም መንገድ፣ የእያንዳንዱ የወንጌል ፀሐፊም የግል ፍላጎትና መሻትም በጻፈው የወንጌል ታሪክ ውስጥ ይንፀባረቃል፡፡ የትኞቹም ሁለቱ እንኳን ፍፁም አንድ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ሁሉም የአዲስ ኪዳን ወንጌላት የሚገልጡት አንዱን ኢየሱስን ነው፣ ሆኖም ስለ እርሱ ግን በተደጋጋሚ የሚናገሩት በተለያየ መንገድ ሲሆን በአገልግሎቱ የተለያዩ ገፅታዎችም ላይ አፅንዖት ይሰጣሉ፡፡

> ***ያሉን አራት ወንጌላት ሲሆኑ፣ ኢየሱስ ግን አንድ ነው፡፡ ያንን ያሰደረገን ምንድን ነው? ከሁሉ አስቀድሞ፣ የቀደሙት ክርስቲያኖች ኢየሱስ በአንድ ገፅታ ብቻ ሊገለፁ የማይችል እጅግ ውስብስብ ታሪካዊ ሰብዕና መሆኑን እውቅና የመስጠት ጠቢብነታቸው ነው፡፡ ወንጌላት የአንድ ሰው ስዕላዊ መግለጫ ዓይነቶች ናቸው፣ በአራቱም ወንጌላት ውስጥ እውቅና የተሰጠው ኢየሱስ ሲሆን፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ባህርያት ውስጥ የተለያዩ ክስተቶችን ከተለያየ ጎን በመመልከት እንዲካተቱ አድርገዋል፡፡ አንድ ምሳሌ እሰጣችኋለሁ፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ፣ በመሠረታዊነት ምሳሌም ሆነ አጋንንትን የማስወጣት ታሪክ የለም፡፡ በማርቆስ ወንጌል ግን፣ ኢየሱስ በርካታ ምሳሌዎችን ሲመስል፣ በማርቆስ ወንጌል የመጀመሪያ ክፍልም ደጋግሞ አጋንንት ሲያስወጣ እናገኘዋለን፡፡ እነዚህ የተለያዩ ሥዕላዊ መግለጫዎች ናቸው ግን የሚገልጡት አንዱን ኢየሱስን ነው፡፡ እናም እያንዳንዱ የወንጌል ፀሐፊ ስለ ኢየሱስ በጥቂቱም***

*ቢሆን ለየት ያለ አመለካከት አለው፡፡ ይህ ማለት ግን አንዱ ክርስቶስ ነው ብሎ ሲያስብ ሌላው ግን አይደለም ብሎ ያስብ ነበር ማለት ሳይሆን፣ ኢየሱስ የአይሁድ መሲህ ደግሞም የዓለም ሁሉ አዳኝ መሆኑን ለመግለጥ የሚያስችሏቸው የተለያዩ አፅንዖቶች ነበሯቸው ማለት ነው፡፡ እናም፣ በመንፈስ ቅዱስ መነዳት ውስጥ ሆነው ስለ ኢየሱስ አገልግሎት የተለያዩ ገፅታዎችን የመፃፍ፣ ጥያቄዎችን በተለያዩ ማዕቀፎች የማስቀመጥና ምላሽ የመስጠት ነፃነቱ ነበራቸው፡፡*

ወንጌላት የየራሳቸው የሆኑ በርካታ ባሕርያትና መሪ ሃሳቦች አሏቸው፡፡ በዚህ የመግቢያ ትምህርት ግን፣ እያንዳንዱ ወንጌል ለሁለት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥበትን መንገድ በመመልከቱ ላይ እናተኩራለን፡፡ እነርሱም፡- "**ኢየሱስ ማን ነው**?" እና "**ኢየሱስን እንዴት እንከተላለን**?" የሚሉ ናቸው፡፡ ማቴዎስ እነዚህን ጥያቄዎች እንዴት እንደሚመልስ በመመልከት እንጀምር፡፡

## በማቴዎስ ኢየሱስ ማን ነው?

ከሁሉም የወንጌላት ፀሐፍት ይልቅ፣ ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን የተነገረለት የእስራኤል መሲሃዊ ንጉሥ መሆኑን በመግለፁ ላይ ያተኮረው ማቴዎስ ነው፡፡

ማቴዎስ የኢየሱስን ንግሥና ከጠቀሰባቸው ስፍራዎች የምንጠቅሰው ናሙና የሚከተሉትን ያካትታል፡ ምዕራፍ 2 ቁጥር 2 ጠቢባኑ "**የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው**?" በማለት በጠየቁት ጥያቄ ውስጥ፤ 7፥21-23 ኢየሱስ አንደ ጌታ፣ በመንግሥተ ሰማያት "**ጌታ**" ያሉትን ሁሉ የማይቀበል መሆኑን ሲናገር፤ 20፥20-28 የያዕቆብና የዮሐንስ እናት በመንግሥቱ ውስጥ ለልጆቿ ከእርሱ ግራና ቀኝ ያለውን ስፍራ እንዲሰጥላት ስትጠይቅ፤ 25፥31-46 በመጨረሻው ቀን እንደ ንጉሥ ስለሚሰጠው ፍርድ ኢየሱስ በተናገረው ምሳሌ ውስጥ፤ 27፥37 በመስቀሉ ላይ ከኢየሱስ አናት በላይ "**የአይሁድ ንጉሥ፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ**" በማለት የሮሜ ወታደሮች የለጠፉትን ማቴዎስ በስላቅ የጠቀሰበት ይጠቀሳሉ፡፡

የእግዚአብሔር መሲሃዊ ንጉሥ መሲሃዊውን መንግሥት ወደ ምድር እንደሚያመጣ ይጠበቃል፡፡ እስራኤልንም ከምርኮኝነቷና ከጠላቶቿ ያድናል፡፡ በጽድቅም ይገዛል፣ ሰላምና ብልጥግናንም ይመሠርታል፡፡ ኢየሱስ እነዚህን ሁሉ አድርጓል፣ ሆኖም አደራረጉ ግን አይሁድ እንደሚጠብቁት አልነበረም፡፡

በማቴዎስ 5፥17 ኢየሱስ የተናገረውን አድምጡ፡

> እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። (ማቴ 5፥17)

ስለ እርሱ አገልግሎት ምስክርነት የሚሰጡ በርካታ አይሁዶች የእግዚአብሔርን ህግ እንደሚሽርና የብሉይ ኪዳንንም ተስፋ ሊፈፅም እንደማይችል እንደሚያስቡ ኢየሱስ ተረድቷል፡፡ ለዚህም ነው

ምንም እንኳን እነርሱን ባይመስላቸውም እርሱ ግን ህግንና ነቢያትን እንደሚፈፅም በፍፁም ግልጥነትና በአፅንዖት የተናገረው፡፡

ኢየሱስ በአንድም ሆነ በሌላ ገፅታ፣ በእውነትም እርሱ የእስራኤል መሲሃዊ ንጉሥ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት የሚናገሩትን ሁሉ፣ እንደፈፀመ ማቴዎስ በዚህ ምንባብ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው ዘግቧል፡፡

እንግዲያው፣ እንደማቴዎስ አገላለፕ፣ ኢየሱስን እንዴት እንከተላለን? ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ሕግ ጠንቅቆ ፈፅሟል፣ ሆኖም ያደረገው ያን ብቻ አልነበረም፡፡ የህጉን ውጫዊ መሻት ብቻ መፈፀም በቂ አለመሆኑን ተናግሯል፡፡ የመንግስቱ ዜጎች ከልባቸው እንዲታዘዙት እግዚአብሔር ዘወትር ይጠብቃል፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ለእግዚአብሔር ህዝብ ምህረትንና ድነትን ይዛ የመጣች፣ ለእኛም አዲስና ታዛዥ ልብ ያስገኘች መሆኗ ወንጌላት የሚያውጁት የምሥራች ነው፡፡ የተለወጠው ልባችንም ኢየሱስን በሚያፈቅር፣ በሚያመሰግንና በደስታ በሚታዘዝ ማንነት የምንከተልበትን ኃይልንና መነሳሳትን ይሰጠናል፡፡

> ***እግዚአብሔርን ከልብ ስለመታዘዝ ስንነጋገር፣ ልብ የሚለው ቃል ሁሉን የሚያካትት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ህዝቤን ሳስተምር ከአእምሮ፣ ወደ ልብ ከዚያም ወደ እጅ እንደሚሄድ እናገራለሁ፡፡ ያም እንዴት ልንታዘዘውና እንዴት ልንወድደው እንደሚገባ ነው፡፡ ጭንቅላት የሃሳብ መቀመጫ፣ የአእምሮ መቀመጫ ነው፣ እናም እግዚአብሔርን በሙሉ ልቡናችን ልንወድደው ይገባል፡፡ በሙሉ ስሜታችን ልንወድደው ይገባል፡፡ በእጎቻችንና በእግሮቻችንም ልንወድደው ይገባል፡፡ ስለዚህ፣ ልብ ማለት በደረታችን ላይ የምትደልቀው ነገር ብቻ አይደለችም፡፡ ሁሉን ያጠቃለለ ቀል ነው፡፡ እግዚአብሔርን በውጫዊ ማንታችን እንወደዋለንን? አዎን እንወደዋለን፡፡ ሆኖም በውስጣዊ ማንነታችንም እንወደዋለን፡፡ እግዚአብሔርን በሁሉም ነገር እንወደዋለን፣ እናም እኔ እንደማምነው "ልብ" የሚለው አባባል ያን ሁሉም ነገር የሚባለውን ያመለክታል፡፡ [ዶ/ር ማት ፍሬድማን]***

ማቴዎስ ሁለቱን ጥያቄዎቻችንን እንዴት እንደመለሰልን ዐይተናል፣ እስኪ ማርቆስ ምን እንደሚል እንመርምር፡፡

## በማርቆስ ኢየሱስ ማን ነው?

አንደኛ፣ እንደ ማርቆስ አገላለጥ፣ ኢየሱስ ማን ነው? ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ህዝብ ጠላቶች ድል የነሳ መከራን የተቀበለው የእግዚአብሔር ልጅ ነው በሚለው ሃሳብ ላይ ማርቆስ ትኩረት አድርጓል፡፡ ኢየሱስ በክፉ ኃይላት ላይ ያለውን ኃይል የሚያመለክቱ ተዓምራቶችን ማርቆስ በብዛት ዘግቧል፡፡ ምንም እንኳን የማርቆስ ወንጌል ከማቴዎስና ከሉቃስ ወንጌላት በጣም አጭር ቢሆንም በድምሩ ዐሥራ ስምንት ተዓምራቶችን ዘግቧል፡፡

ኢየሱስ ድል ነሺውና መከራን የሚቀበለው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የምናየው ገና በማርቆስ ወንጌል ጅማሬ ላይ ነው፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ እኳን፣ መጥምቁ ዮሐንስ የኢየሱስን መምጣት ይተነብይና እዚያው ኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎቱን ይጀምራል፡፡ ይጠመቃል፣ በዲያቢሎስ

ይፈተናል፣ የመጀመሪያዎቹን ደቀመዛሙርቱን ይጠራል፣ ክፉ መናፍስትን ያስወጣል፣ በርካታ ሰዎችንም ከተለያዩ ደዌዎች ነፃ ያወጣል፡፡ ይህን በተግባር የታጨቀ፣ ፈጣን የሰደድ እሳት መሳይ ትረካ ላይ ላዩን ለሚያነብበው እንኳን ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጠላቶች በኃይል ድል የነሳ መሆኑን ያሳየዋል፡፡ በጥልቀት በሚደረገውም ንባብ፣ እርሱ መከራን የሚቀበለው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ማርቆስ መግለጡን ማየት ይቻላል፡፡

ለምሳሌ፣ በማርቆስ 1፥12-13 የኢየሱስን መጠመቅ ተከትሎ የሆነውን ነገር እንመለከታለን፡

> ወዲያውም መንፈስ ወደ ምድረ በዳ አወጣው።
> በምድረ በዳም ከሰይጣን እየተፈተነ አርባ ቀን ሰነበተ ከአራዊትም ጋር ነበረ፥
> መላእክቱም አገለገሉት። (ማር 1፥12-13)

ኢየሱስ ገና በአደባባይ አገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ የሰይጣን ብርቱ ጥቃት አርፎበታል፡፡ ይህ ኢየሱስን መከራን እንደሚቀበለው አገልጋይ የመግለጡ የማርቆስ ዘገባ በወንጌሉ ውስጥ እያደገ የሚሄድ ሲሆን ይህም ኢየሱስ መከራንና መናቅን በመታገሱ ተገልጧል፡፡

እንግዲያው፣ ማርቆስ ኢየሱስን እንዴት አንድንከተል ነው የሚነግረን፣ መከራን እንደተቀበለው ድል ነሺ? በአንድ በኩል፣ የማርቆስ ወንጌል የክርስትናን ሕይወት የጣፋጭነት ቅብ አይቀባትም፡፡ ማርቆስ ደቀመዝሙርነትን የሚገልጠው እጅግ አስቸጋሪ፣ ተስፋ አስቆራጭና መከራን የምንቀበልበት ብቻ ሳይሆን ስህተት የምንፈፅምበትና የምንወድቅበትም እንደሆነ ነው፡፡ በመሠረቱ፣ የማርቆስ ወንጌል መለያው የኢየሱስ ደቀመዛሙርት እርሱን ሊረዱት ወይም ሊያምኑት አለመቻላቸውን መግለጡ ነው፡፡ በማርቆስ 4፥40 ላይ፣ ደቀመዛሙርቱ በእርሱ ስለማመናቸው ኢየሱስ ተደንቋል፤ በምዕራፍ 6 ቁጥር 52፣ የደቀመዛሙርቱ “**ልባቸው ደንዝዞ ነበር**”፤ በ7፥18፣ ደቀመዛሙርቱ ትምህርቶቹን “**ባለማስተዋላቸው**” ነቅፏቸዋል፤ በ9፥18 ደቀመዛሙርቱ ክፉ መንፈስ ማስወጣት ሳይችሉ ቀርተዋል፤ በ9፥38-41፣ ደቀማዛሙርቱ አንድን ሰው ስለማያውቁት ብቻ አጋንንት እንዳያስወጣ ከልክለው ነበር፤ በምዕራፍ 14 ውስጥ፣ አንዱ ደቀመዝሙር ኢየሱስን አሳልፎ ሰጠው፣ አንዱ ደግሞ አላውቀውም ብሎ ካደው፣ የተቀሩት ደግሞ ጥለውት ሸሹ፡፡

በማርቆስ ወንጌል የምንመለከተው ይህ አፅንዖት ኢየሱስን ስለ መከተል ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ያስተምረናል፡፡ አንደኛ፣ ልክ እንደ ደቀመዛሙርቱ፣ ኢየሱስን ዘወትር ልንረዳው አንችልም፡፡ በመሠረቱ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምንስታቸው ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ስለዚህ፣ ሁላችን ገና ልንማር የሚገባን ብዙ እንደሆነ ለማወቅ ትሁት መሆን ይገባናል፡፡ ምን እንኳን ለእኛ እንግዳና ስህተት ቢመስለንም የመጽሐፍ ቅዱሱን አስተምህሮ እውነት መሆኑን በእምነት ልንቀበል ይገባናል፡፡

ሁለተኛ ደግሞ፣ መከራና ችግር ለክርስቲያኖች አይቀሬ ናቸው፡፡ እርሱን ከመከተል ዘወር የሚያደርጉ ብዙ አደጋዎችና ብዙ ፈተናዎች አሉ፡፡

በማርቆስ 8፥34-35 ኢየሱስ የተናገረውን አድምጡ፡

> ሕዝቡንም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ጠርቶ እንዲህ አላቸው፡- በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ። ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፥ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን ያድናታል። (ማር 8፥34-35)

ለእርሱ ባለን መሰጠት ታማኞች ልንሆን እንደሚገባ ኢየሱስ አስተምሮናል፡፡ ኢየሱስ እንደተሰቃየ ንልሰቃይ፣ በመከራና በመንፈሳዊ ጥቃት ውስጥ ፀንተን ልንቆም ይገባናል፡፡ በዚህ ምንባብ ውስጥ አንድ ሌላም ነገር ልብ በሉ፡ ኢየሱስ መከራን የሚቀበለው የእግዚአብሔር ልጅ ብቻ ሳይሆን፤ ድል ነሺውም የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡ በመሠረቱ፣ ድል የነሳው በጣዕር ሞቱ ነው፡፡ ስለ መንግሥቱ መከራን በመቀበል እርሱን በታማኝነት ከተከተልነው፣ የዘላለምን ሕይወት ብድራት እንቀበላለን፡፡

> *መከራ በእውነት አስፈላጊ በሆነው ነገር ላይ ንቁ እንድንሆን ያደርገናል፤ ከስቃዩ የተነሳ፣ ጉዳዩ አሁን የምናየው ብቻ እንዳልሆነ እንድንገነዘብ ያደርገናል፡፡ ልኖርለት የሚገባ ሌላ አንድ ክቡር ነገር መኖሩን፣ እኔ ግድ ከምሰኝባቸው ከራሴ ደስታ፣ ከራሴ ምቾትና ዋስትና ይልቅ በክርስቶስ ያገኘሁት ነገር እጅግ የላቀ መሆኑን በመከራው መካከል ውስጥ እግዚአብሔርን በመታመን እመለከታለሁ፡፡ [ዶ/ር ጆን ማኪንሌይ]*

> *ኢየሱስ መከራን እንደሚቀበል አገሊጋይ መጥቷል፡፡ ክርስቶስን የሚከተል ሰውም ትርጉም ላለው መከራ በሕይወቱ ስፍራ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ ነገር በኢየሱስ ማንነት ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያለው ነገር ሲሆን ወደ ዓለም ሲመጣ መከራን ተሞልቶ ነበር፣ የክርስቶስ አገልግሎት አካሎች ከሆንን፣ በሕይወታችን ለመከራ ስፍራ ሊኖረን ይገባል፡፡ የራሳችን መከራ ብቻ ሳይሆን፣ የሎሎችንም መከራ መካፈል ማለትም፣ ከሚያለቅሱ ጋር ማልቀስ እና የጉዳዩ አካል ሆነን በዚያው አውድ ማገልገል ይገባናል፡፡ የእግዚአብሔርን ልብ መረዳት የምንጀምረው፣ ወደዚህ ዓለም ስንመጣና የዚህ የመከራ አካላት መሆናችንን ስንረዳ፣ እንደ ክርስቶስ ተከታዮች በዚህ መንገድ እንድናገለግል እግዚአብሔር ከሚፈልግባቸው መንገዶች አንዱ መሆኑን ስናውቅ ነው፡፡ ያኔ፣ እግዚአብሔር ያጠራናል፡፡ መከራ ባህርይን ይቀርፃል፣ ተስፋንም ይፈነጥቃል፣ ፅናትንም ይሰጠናል፡፡ ስለዚህ በሌሎች መንገዶች ከሚሠራው ይልቅ በብዙ መከራ ውስጥ፣እግዚአብሔር ሕይወታችንን በማጥራት ሲሠራ እናየዋለን፡፡ [ዶ/ር ኬ.ኤሪክ ቶኔስ]*

ማቴዎስንና ማርቆስን በልቡናችን ይዘን፣ ሉቃስ ደግሞ ስለ ኢየሱስና ስለተከታዮቹ የሚሰጠንን ምላሽ እንመልከት፡፡

## በሉቃስ ኢየሱስ ማን ነው?

የሉቃስ ወንጌል "**ኢየሱስ ማን ነው?**" የሚለውን ጥያቄ የሚመልሰው እርሱ ርኅሩኅ የዓለም አዳኝ የሚለውን በማወጅ ነው፡፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ድነት ለሃብታሙም ለድሃውም፣ ለሃይማኖት መሪዉም ማኅበረሰብ ለገፋውም ሁሉ አምጥቷል፡፡ የኢየሱስ የምሥራች ለሁሉ ማለትም አስታዋሽ ለሌላቸውና ለተናቁትም ሁሉ ነው፡፡ ሉቃስም ይህንን በብዙ መንገድ አፅንዖት ሰጥቶታል፡፡ በርካታ ወንዶች ሴቶችን የበታች በሚያደርጉበት ወቅት ኢየሱስ እህትማማቾቹን ማርያምንና ማርታን ከበሬታ ሰጥቷቸዋል፡፡ ሽባ፣ ህመምተኛ፣ እንዲያውም አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች የተመሰገኑበትንና ሰዎች ተምሳሊት ሊያደርጓቸው የሚገቡ ምሳሌዎችንና ትረካዎችን ዘግቧል፡፡ በቤተመቅደስ ኑሮዋን ሁሉ የሰጠችውን መበለት ኢየሱስ አመስግኗታል፡፡ ለሉቃስ ወንጌል አንባቢዎች በጠቅላላ ተምሳሊት ሊሆን የሚችለውንና በማኅበረሰብ የተገፋውን የቀረጥ ሰብሳቢውን የዘኪዎስን ታሪክ ሉቃስ ይነግረናል፡፡ ደግሞ ደጋግሞ፣ ማኅበረሰብ ስላገለላቸውና ስለናቃቸው ሰዎች ኢየሱስ ግድ መሰኘቱን ሉቃስ ዘግቧል፡፡

አንዱን ለምሳሌ ለማንሳት፣ በሉቃስ 7፥12-16 የተጻፈውን አድምጡ፡

> ወደ ከተማይቱም በር በቀረበ ጊዜ፥ እነሆ፥ የሞተ ሰው ተሸከመው አወጡ፤
> እርሱም ለእናቱ አንድ ልጅ ነበረ፥ እርስዋም መበለት ነበረች፥ ብዙም የከተማ
> ሕዝብ ከእርስዋ ጋር አብረው ነበሩ።
> ጌታም ባያት ጊዜ አዘነላትና። አታልቅሽ አላት።
> ቀርቦም ቃሬዛውን ነካ፥ የተሸከሙትም ቆሙ፤ አለውም። አንተ ጐበዝ፥
> እልሃለሁ፥ ተነሣ።
> የሞተውም ቀና ብሎ ተቀመጠ ሊናገርም ጀመረ፥ ለእናቱም ሰጣት።
> ሁሉንም ፍርሃት ያዛቸውና። ታላቅ ነቢይ በእኛ መካከል ተነሥቶአል፥ ደግሞ።
> እግዚአብሔር ሕዝቡን ጐበኘ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ።
> (ሉቃስ 7፥12-16)

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የሮማውያን ዓለም፣ ወንድ ልጇን ያጣች መበለት ሥራ የማግኘትና ለኑሮ የሚያስፈልጋትን መግቦት የማግኘት ዕድሏ ጠባብ ነው፡፡ ሉቃስ ኢየሱስ ለእርሷ ባሳየው ርኅራኄ ላይ አፅንዖት በመስጠት፣ የጌታ የማዳን ሥራ ድሆችንና ተስፋ የሌላቸውን ዒላማ ያደረገ መሆኑን አመልክቷል፡፡ በድርጊቱ ፍፃሜ ላይ ሰዎች አስተያየት ሲሰጡ፣ ለተቸገሩና አቅም ለሌላቸው ኢየሱስ የሚሰጠው አገልግሎት እግዚአብሔር ህዝቡን የጎበኘ መሆኑ ማስረጃ ነው ብለዋል፡፡

እንግዲያው፣ ሉቃስ ኢየሱስን እንዴት እንከተለውን የሚለውን ሁለተኛ ጥያቄ የሚመልሰው እንዴት ነው? ሉቃስ ለድሆች ያለውን ትኩረት በመቀበል፣ ለሌሎች መራራት ይገባናል፡፡ ድሆችን ልንከባከብ እና መሻቶቻቸውን የማሟላት ጉጉት ሊኖረን ይገባል፡፡ ካለን ጥሪት፣ ከምግባችን፣ ከገንዘባችንና ከጊዜያችን ልናካፍላቸው ይገባል፡፡ በመሠረቱ፣ እግዚአብሔር ለችግረኞች ልመና መልስ የሚሆኑ በጎ አድራጊ ክርስቲያኖችን እግዚአብሔር ደጋግሞ ያስነሳል፡፡

በሉቃስ 12፥33 ኢየሱስ እንደተናገረው፡

> ያላችሁን ሽጡ ምጽዋትም ስጡ፤ ሌባ በማይቀርብበት ብልም በማያጠፋበት በሰማያት የማያልቅ መዝገብ የሚሆኑትን የማያረጁትንም ኮረጆዎች ለራሳችሁ አድርጉ፤ (ሉቃስ 12፥33)

የእርሱን ህዝብ በመንከባከብ ኢየሱስን በእውነት ስንከተለው፣ በዘላለማዊ ብድራት ይባርከናል፡፡

ኢየሱስን የምንከተልበት ሌላው መንገድ እግዚአብሔር መሻታችንን የሚያሟላ መሆኑን በመረዳት ያለስጋት በማረፍ ነው፡፡ ኢየሱስ በሉቃስ 12፥22-31 የተናገረውን አድምጡ፡

> ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አለ፦ ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ለነፍሳችሁ በምትበሉት
> ወይም ለሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ።
> ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ ይበልጣልና።
> ቍራዎችን ተመልከቱ፤ አይዘሩም አያጭዱምም፥ ዕቃ ቤትም ወይም ጎተራ
> የላቸውም፥ እግዚአብሔርም ይመግባቸዋል፤ እናንተስ ከወፎች እንዴት
> ትበልጣላችሁ?
> ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው?
> እንግዲህ ትንሹን ነገር ስንኳ የማትችሉ ከሆናችሁ፥ ስለ ምን በሌላ ትጨነቃላችሁ?
> አበቦችን እንዴት እንዲያድጉ ተመልከቱ፤ አይደክሙም አይፈትሉምም፤ ነገር ግን
> እላችኋለሁ፥ ሰሎሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከእነዚህ እንደ አንዲቱ አለበሰም።
> እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን በሜዳ የሆነውን ሣር
> እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ፥ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ እናንተንማ ይልቁን
> እንዴት?
> እናንተም የምትበሉትን የምትጠጡትንም አትፈልጉ፥ አታወላውሉም፤
> ይህንስ ሁሉ በዓለም ያሉ አሕዛብ ይፈልጉታልና፤ የእናንተም አባት ይህ
> እንዲያስፈልጋችሁ ያውቃል።
> ዳሩ ግን መንግሥቱን ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል። (ሉቃስ 12፥22-31)

እንደ እግዚአብሔር መንግሥት አባላት፣ ታላቁ ንጉሣችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ያስባል ፍላጎታችንንም ያሟላል ብለን ልንተማመን ይገባናል፡፡

ይህ በአዳኙ የመታመን ነገር በሉቃስ ወንጌል ከተጠቀሱ ከሌሎች ሁለት መሪ ሃሳቦች፡ ሰላምና ደስታ ጋር በቅርብ ይዛመዳል፡፡ ለምሳሌ፡ በሉቃስ ወንጌል ጅማሬ በምዕራፍ 2፥10-14 ላይ፣ ይህንን የመላእክት አዋጅ እናነባለን፡

> እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና... ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ። (ሉቃስ 2፥10-14)

ከሃያ ሁለት ምዕራፎች በኋላም፣ ሉቃስ ወንጌሉን በጀመረበት መንገድ ይደመድመዋል፡፡ በታሪኩ ማብቂያ ላይ፣ መላእክቱ በምዕራፍ ሁለት የተነበዩትን ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስን በመከተል ደስታን ያጣጥማሉ፡፡

*በዮሐንስ 20 ውስጥ፣ ኢየሱስ ባደረገው ንግግር ለሦስት ጊዜያት **"ሰላም ለእናንተ ይሁን"** ሲላቸው ሃይ ማለቱ ብቻ ነው ብዬ አላስብም፡፡ እያለ ያለው የእውነታው መሠረት ይህ ነው ማለቱ እንደሆነ አስባለሁ፡፡ ምንም እንኳን አሁን በችንቅ ውስጥ ብታልፉም፣ የምትወዱትን ብታጡም፣ ለለመለስ የምሄድ መሆኔን ባታውቁም፣ በሮማውያን የጭቆና አገዛዝ ስር ፈጥናችሁ ብትወድቁም፣ በጭቆና ስር ብትወድቁም፣ ነገሩ እየከፋ ቢሄድም፣ እኔ እዚህ እንዳለሁ እንድታውቁ፣ እዚህ ካለሁም መሠረታዊ ሰላም የማመጣ መሆኑን እንድታውቁ እፈልጋለሁ፡፡ እኔ ደስታችሁ ነኝ፡፡ እንግዲያው፣ ምንም ይሁን ምን፣ በውጪው ሕይወታችሁ የፈለገው ይምጣ፣ በውስጣዊ ሕይወታችሁ ምንም ይሁን ምን፣ እኔን ካወቃችሁ፣ እውነተኛና መሠረታዊ ሰላም አላችሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃሉ **"ሻሎም፣"** ያም ማለት ምንም እንኳን ጦር ቢሰበቅ የእግዚአብሔር ንግሥናና አገዛዝ ሁነልንታዊ ጽድቅን ያመጣል ማለት ነው፡፡ እኔም ደስታን አመጣለሁ፡፡ እዚህ ያለሁት ላባብላችሁ አይደለም፡፡ በዚህ ያለሁት ከስሜት የዘለለ ደስታ፣ እውነተኛን ደስታ ላመጣላችሁ ነው፡፡ ያም ደስታ ዓለምን የምቆጣጠር መሆኔን እናም አስቀድሞ በእኔ ያልደረሰው እንደማይደርስባችሁ፣ በቀና መልክ የምትረዱበት ደስታ ነው በማለት ኢየሱስ ተናግሯል፡፡ ጳውሎስ ስለ መንፈስ ፍሬ ሲናገር ያስቀመጠበትን መንገድ እወደዋለሁ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቲያኖች ሕይወት በሙላት ሲመጣ፣ ፍቅርን ትሞላላችሁ፣ ቀጣዩ ቃል ደግሞ በደስታ ትሞላላችሁ ይላል፡፡ እንደማስበው እነዚህ ሁለቱ አይነጣጠሉም፡፡ እርግጥ ነው ሌሎች ሰድስት ነገሮችን ጨምሯል፣ ዋናው ግን የእግዚአብሔር ፍቅር በልቤ ሲፈስ ወይም ሲመጣ፣ ስለ እውነታዎች ባለኝ የግል መረዳቱ አልኖርም፣ ያ ከሆነ ጥርጣሬ ነው፣ ጨለምተኝነት ደግሞም አፍራሽ ነው፡፡ ኢየሱስ ባለበት፣ ብቸኛው ምላሽ፣ ሰላም ማግኘቱ ነው፡፡ የእርሱን የትንሣኤ ኃይል ወደ እኔ ያመጣል፣ እናም ደስ ይለኛል፣ ተስፋ አለኝ፣ ምክንያቱም በኢየሱስ ሽንፈት የለምና፡፡ ነገሮችም **"አይበታተኑም"** በሙላትና በፍፁምነት ሁሉን ያገጣጥማቸዋል፡፡ **[ዶ/ር ቢል ዑሪ]***

በምዕራፍ 24፥52-53 የሉቃስን የመጨረሻ ቃሎች አድምጡ፡

> እነርሱም፤ ሰገዱለትና በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፥
> ዘወትርም እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እየባረኩ በመቅደስ ኖሩ። (ሉቃስ 24፥52-53)

በሉቃስ ወንጌል፣ ኢየሱስን መከተል ማለት በመዳናችን እና በእግዚአብሔር በረከቶች ደስ መሰኘት፣ በሰላም በእርሱ ማረፍ፣ መሻታችንን እንደሚያሟላ በእርሱ መታመን፣ እነዚህም በረከቶች ለሌሎች እንዲደርሱ እርሱ እንዲጠቀምብን መፍቀድ ማለት ነው፡፡

ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ "ኢየሱስ ማን ነው?" "እርሱን እንዴት እንከተለዋለን?" ለሚሉ ጥያቄዎች የሰጡትን ምላሽ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ዮሐንስ ለየት ባለ መንገድ እንዴት እንደመለሰ እንመለከታለን፡፡

## በዮሐንስ ኢየሱስ ማን ነው?

ዮሐንስ በወንጌሉ ኢየሱስን የገለፀው፣ የዘላለምን ድነት እቅድ እንደፈፀመ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡ በኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅነት ላይ አፅንዖት በመስጠት፣ ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ስላለው ለየት ያለ ግንኙነት ዮሐንስ ተናግሯል፡፡ ኢየሱስ ብቸኛው የአብ የመጨረሻው መገለጥና እምነታቸውን በእርሱ ላይ ላደረጉ የዘላለምን ሕይወት መስጠት የሚችል ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ቀሪዎቹ ሦስት ወንጌላት ታሪኩን ከኢየሱስ ልደት ወይም ከምድራዊ አገልግሎቱ ሲጀምሩ፣ ዮሐንስ ግን ወንጌሉን የሚጀምረው የእግዚአብሔር ልጅ ከአብ ጋር በመፍጠር ሥራ አብሮ የነበረ እና አሁን ደግሞ አብ በአንድያ ልጁ በኩል ራሱን የገለጠ መሆኑን በመናገር ነው፡፡

ዮሐንስ ይህንን የከበረ መልእክቱን ያስተላለፈበት ሌላው መንገድ ኢየሱስ “እኔ ነኝ” ብሎ የተናገረባቸውን በመጥቀስ ነው፡፡ በነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ኢየሱስ የጠቀሰው “ያህዌ” የተሰኘውን አንዳንዴም “ይሖዋ” ተብሎ የሚተረጎመውን የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ስም ነው፡፡ በዘፀአት 3፥14፣ እግዚአብሔር ራሱ “ያህዌ” የሚለው ስም “እኔ ነኝ” ማለት መሆኑን ገልጧል፡፡ ኢየሱስም በዮሐንስ 6፥35 “የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ” በማለት ጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም በ8፥12 እና በ9፥5 ውስጥ “የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ፡፡” በ10፥7፣9 ውስጥ “እኔ በር ነኝ፡፡” በ11፥25፣ “ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፡፡” በ14፥6 “እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፡፡” በ15፥1 “እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ” የሚሉትን እናገኛለን፡፡ በ8፥58 ውስጥ ደግሞ፣ ኢየሱስ “እኔ ነኝ” የሚለውን ከፍተኛ አዋጅ አውጇል፡፡ በሁሉም ውስጥ፣ በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር የተሰጠውን ቅዱስ ስም የያዘና እግዚአብሔርንም የገለጠ መሆኑን አውጇል፡፡

ኢየሱስ የእግዚአብሔር የዘላለም የድነት እቅድ መካከለኛ መሆኑ በግልፅ የተመለከተው በዮሐንስ 17 ውስጥ በተጠቀሰው ሊቀ ካህናዊ ጸሎት ውስጥ ነው፡፡ በዮሐንስ 17፥24 ኢየሱስ የጸለየውን አድምጡ፡፡

> አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር ስለ ወደድኸኝ የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ። (ዮሐ17፥24)

ኢየሱስ የእርሱን ተከታዮች ድነት ዓለም ሳይፈጠር አብ ለልጁ ከነበረው ፍቅር ጋር አገናኝቶታል፡፡ ነጥቡም መዳናችን እግዚአብሔር ለኢየሱስ ካለው ፍቅር የመነጨ መሆኑ ነው፡፡

እንግዲያው፣ ዮሐንስ ኢየሱስ የዘላለምን የድነት እቅድ የፈፀመ መሆኑን ከገለፀ፣ የዮሐንስ ወንጌል ሁለተኛውን ጥያቄአችንን የሚመልሰው እንዴት ነው? ኢየሱስን እንዴት እንከተል?

በዮሐንስ ወንጌል፣ ኢየሱስን የምንከተልበት ቀዳሚ መንገድ በእግዚአብሔር በመወደድ እና ያንንም ፍቅር ለእርስ በርሳችን በመግለጥ ነው፡፡ በበርካታ መንገዶች እንገልፅው ዘንድ ኢየሱስ ይህንን ተምሳሊት አሳይቶናል፡፡ ለምሳሌ፣ ኢየሱስ በዮሐንስ 17፥23-26 አብ ለወልድ ስላለው ፍቅር በተናገረበት ውስጥ እናየዋለን፡፡ ኢየሱስ ከፈፀመው የዘላለም ድነት እቅድ ጀርባ ያለው ይህ አብ ለወልድ ያለው ዘላለማዊ ፍቅር ነው፡፡ እንግዲያው፣ ደቀመዝሙርነት በዮሐንስ ወንጌል ከፍቅር ጋር ተያይዞ መገለጡ ትርጉም ይሰጣል ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ለተከታዮቹ በዮሐንስ 13፥34-35 ፡

እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።
እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ። (ዮሐ 13፥34-35)

እንደ ዮሐንስ አገላለጥ፣ የእርሱን በሚመስል ፍቅር በመዋደድ ኢየሱስን እንከተለዋለን፡፡

በዚህ መንገድ፣ ደቀመዝሙርነት የሚነሳሳውም ሆነ የሚገለጠው በፍቅር ነው፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር ደቀመዝሙርነትን ያነሳሳዋል፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ውስጥ ለእርስ በርሳችን ሲገለጥ ደቀመዝሙርነታችን ይገለጣል፡፡ ይህም ዮሐንስ በወንጌሉ ራሱን **"የተወደደው ደቀመዝሙር"** ከማለት ይልቅ **"ኢየሱስ ይወደው የነበረ ደቀመዝሙር"** በማለት ለምን እንደገለጠ እንድንረዳ ያግዘናል፡፡ እርሱ ያለው ሌሎችን የመውደድ ችሎታ ኢየሱስ ለእርሱ ካለው የፍቅር ጥልቀት ብቻ ሊመጣ የሚችል መሆኑን ያውቃል፡፡ የኢየሱስ ተከታዮች አስቀድመው የተወደዱና እርስ በርሳቸውም እንዲዋደዱ የጠጠሩ ናቸው፡፡

**በአራቱ ወንጌላት መካከል ያለው የየራሳቸው መለያ እርስ በርስ የማይጣጣሙና የሚቃረን ታሪክ የዘገቡ መስሎት አንድ ሰው ግራ ቢጋባ፣ ጉዳዩ ግን ፈፅሞ እንደዚያ እንዳልሆነ አስባለሁ፡፡ እኔ እንደማስበው በአራቱ ወንጌላት የተገለጡት ስለ ኢየሱስ የሚጣጣሙ አራት አመለካከቶች ናቸው፡፡ አራቱም ወንጌላት ትስጉተ እግዚአብሔር ስለሆነው፣ ኃጢአተኞችንም ከኃጢአትና ከሞት ሊያድን ወደ ዓለም ስለመጣው ስለ አንዱ ሰው ታሪክ የሚነግሩን የሚጣጣሙ ወንጌላት ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸውም ያንን ኢየሱስን በተለያየ አመለካከትና በሕይወቱም ስለተከናወኑ ነገሮች የተለያዩ አፅንዖቶችን በመስጠት ተመልክተውታል፣ ሆኖም እነዚህ መልእክቶችና አስተሳሰቦች ግን የሚቃረኑ ሳይሆኑ የሚመጋገቡ ናቸው፡፡ [ዶ/ር ስቲቭ ኮዋን]**

# ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት፣ የወንጌላት ጥናት መግቢያን አይተናል፡፡ ወንጌላት ተዓማኒ ታሪካዊ ትረካዎች የመሆናቸውን ስነ-ጽሑፋዊ ባሕርይ ተመልክተናል፡፡ ባለሥልጣን የሆኑት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ክፍል መሆናቸውን በመመልከት፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያላቸውንም ስፍራ አስተውለናል፡፡ ምንም እንኳን ደቀመዝሙርነትንና ኢየሱስን በየራሳቸው መንገድ ቢገልጡም፣ ሁሉም ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ተመሳሳይ ታሪክ የዘገቡ መሆኑን አንዳቸውን ከሌላቸው በማስተያየት ተመልክተናል፡፡

ወንጌላትን መረዳት ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ወሳኝ ነው፡፡ የዚህን ምድርም ሆነ የሚመጣውን ሕይወታችንን ፊት ለፊት አይተነው በማናውቀው በኢየሱስ እጅ ላይ አሳርፈናል፡፡ ስለ እርሱ የምናውቀው በቃሉ ብቻ ነው፣ በተለይም በወንጌላት፡፡ በዚህ መግቢያ ላይ ያገኘነው ትምህርት፣ የእያንዳንዱ ወንጌላዊ መልእክት በእምነትና በሕይወታችን ላይ እንዴት ተፅዕኖ እንደሚፈጥር ለመረዳት እንችል ዘንድ አራቱንም ወንጌላት በጥልቀት ለመመልከት ያዘጋጀናል፡፡